# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 016 መስከረም 16 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “የመውሊድ በዓልን ስናከብር የትህትና መንገዶችን በማሰብ ሊሆን ይገባል”

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የመውሊድ በዓልን ስናከብር የነቢዩ መሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) በረከቶች በማስተዋልና የትህትና መንገዶችን በማሰብ ሊሆን ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመውሊድ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በመልዕክታቸው የየትኛውም እምነት ተከታዮች የሆንን ኢትዮጵያውያን፣ በዚህ ታላቅ በዓል ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር አንድ ሆነን ትህትናን፣ ደግነትንና ይቅር ባይነትን ገንዘባችን በማድረግ፣ መንፈሳዊ ሕይወታችንን እናበለጽጋለን ብለዋል።

ትህትና፣ ደግነትና ይቅር ባይነት የማይፈቱት ችግር የለም፤የማያሻግሩት ወንዝ የለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አንድ ሆነን፣ በፍቅርና በሰላም እናድጋለን ሲሉ በመልዕክታቸው ገልጸዋል።

በዓሉን ስናከብር የነቢዩ መሐመድን በረከቶች በማስተዋልና የትህትና መንገዶችን በማሰብ ማሳለፍ ይገባል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳመለከቱት፤ ትህትና፣ ደግነትና ይቅር ባይነት ብዙዎቹን ችግሮች ይፈታሉ፤ ብዙ ይቅርታዎች ብዙ ርቀት ወደፊት ያራምዳሉ፡፡

ትሁት ብንሆን፣ ብርሃን ይታየናል፡፡ ደግ ብንሆን፣ መንገዱን እናገኘዋለን፡፡ ይቅር ባይ ስንሆን፣ መሻገሪያው ይታየናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አመላክተዋል፡፡

በየቦታው የሚነሱ አንዳንድ ችግሮችን እያየ፣ ሁሉ ነገር ጨለማ የሚመስለው ወገን አለ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከየትኛውም ጨለማ በኋላ ግን ብርሃን አለ! ከየትኛውም ቋጥኝ እና ተራራ ባሻገር መንገድ አለ፡፡ ወንዙ፣ መሻገሪያ አለው፣ አቀበቱ ቁልቁለት አለው ብለዋል፡፡


**“የመውሊድ በዓልን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**











# ‘ማርያምን’ እና ‘ወላሂ’ እኩል የሚታመንበት ቤት

**ዳግማዊት ግርማ**

ይህ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው:: ሀገሪቱ የመቻቻል ደሴት የመዋደድ ዓለም ናት:: በአብሮነት ልኬት የሞላ መኖርን ታድላለች:: የነእስማኤልን ቤት ማፍጠሪያ በልቶ ይስሀቅ ይጠግባል:: በነሙሴ የሚካኤል ፃዲቅ ሙሳ ርሀቡን ያስታግሳል:: እዚህ እንደዚህ ነው:: አንዳቸው ለሌላቸው ሲሉ ምንም ያደርጋሉ:: የአንዳቸውን በዓል ማክበሪያ ሌላኛቸው ያጸዳሉ:: በዚህችው ቅድስት ሀገር ውስጥ ክርስቲያኑ የሙስሊሙን ቆብ ይሰፋል:: ሙስሊም የክርሲያኑን የአንገት ክር ይገምዳል:: እነአብርሃም የእማማ ፋጤን ልጆች ደግሰው ይድራሉ:: አባ ቄሱ ለታመሙት የነሙሀመድ ልጆች መዳን ጾመው ይጸልያሉ::

ሀገሪቷ ተዋዶ ያለበት እስላም ክርስቲያኑ ተብላ በከያኒው አፍ ተንቆለጳጵሳለች:: ኢትዮጵያ በሙስሊም ክርስርቲያኑ ተወዳሽ ሀገር ናት:: እንደ ዛሬ ባለው ወቅት ደግሞ የሁለቱ እምነት በዓላት አንድ

**‘ማርያምን‘ እና” ወሳሂ‘ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**






# የመስቀል ደመራና የመውሊድ በዓላት በሰላም እንዲጠናቀቁ በቂ ዝግጅት ተደርጓል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የመስቀል ደመራ እና የመውሊድ በዓላት በሰላም እንዲጠናቀቁ በቂ ዝግጅት ማድረጉን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ገለጸ።

ግብረ-ኃይሉ በላከው መግለጫ፤ ለመላው ሕዝበ ክርስቲያንና ለመላው ሕዝበ ሙስሊም እንኳን ለመስቀል ደመራና ለመውሊድ በዓላት በሰላም አደረሳችሁ በማለት

**የመስቀል ደመራና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የመውሊድና የደመራ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ጽዳት ተካሄደ

ገጽ 4









# ኢትዮ ቴሌኮም የእሳትና አደጋ ስጋት አመራርን ለማዘመን የሚያስችል ስምምነት ተፈራረመ

ሞገስ ጸጋዬ




አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም ስማርት የእሳትና አደጋ ስጋት አመራር ፕሮጀክትን እውን ለማድረግ የሚያስችለውን ስምምነት ከአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በትናንትናው ዕለት ተፈራረመ፡፡

በስምምነቱ ወቅት በኢትዮ ቴሌኮም የቴክኖሎጂ ዘርፍ ዋና ኃላፊ አቶ ታሪኩ ደምሴ እንደገለጹት፤ የስማርት የእሳትና አደጋ ስጋት አመራር ፕሮጀክት በእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የቴክኖሎጂ አተገባበር ተግዳሮቶችን ለመፍታት፣ የተቀናጀ የግንኙነት ሥርዓት ለመተግበር፣ አካባቢያዊ የመረጃ ሥርዓት ለመዘርጋትና አስፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ ለማዋል ይረዳል፡፡

በተጨማሪም ስምምነቱ ወደ ተግባር ሲገባ ውጤታማ የአደጋ ጊዜ ሥራ አመራርን ለመደገፍ፣ የመስክ ምላሽ ሰጪ ተሽከርካሪዎችን በአካባቢያዊ መልኩ ለማቀናጀት፣ የመስክ የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰራተኞች ስልኮችን ከሞባይል መተግበሪያ ጋር እንዲናበቡ በማድረግ በማንኛውም ጊዜ ከድንገተኛ አደጋ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለማቀላጠፍና አደጋዎችን በቀላሉ ለመቆጣጠር እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ታሪኩ ገለጻ፤ በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረገው ስትራቴጂያዊ ስምምነት የአደጋ ጊዜ ድጋፍ አሠጣጥን በማዘመን የአደጋ መረጃ ፈጣን እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ጉዳቶችን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ የሚያስችል ነው፡፡ በተለያዩ ቦታ የሚገኙ ቅርንጫፎች ከዋናው ማዕከል ጋር ፈጣን ግንኙነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ ወጭ ቆጣቢ አሰራር ለመተግበርና የርቀት የአደጋ ጊዜ ድጋፍ እውን ለማድረግ እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

በስምምነቱ መሰረት ኢትዮ ቴሌኮም ከድህረ ትግበራ በኋላ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል ያሉት አቶ ታሪኩ፤ የተሟላ የአደጋ ጊዜ የጥሪ ማዕከል አገልግሎትና የአደጋ ጊዜ መገናኛ ማዕከልን እውን በማድረግና በመምራት አገልግሎቱን በጥራትና በቅልጥፍና ያቀርባል፡፡ ቀጣይ የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር አገልግሎትን ለማዘመን ኢትዮ ቴሌኮም ሁሉን አቀፍ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ አገልግሎቶች ለማቅረብ የተከላ ሙከራ፣ የስልጠናና ቀጣይነት ያለው የድህረ ትግበራ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሰለሞን አማረ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ የአዲስ አበባን የእሳትና አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽንን ለማዘመን ይረዳል፡፡ ኮሚሽኑ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ ለውጦችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ፈጣንና ውጤታማ በሆነ መንገድ ኅብረተሰቡን ለመከላከል የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ አደጋዎች ሲያጋጥም፣ በአፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ የሚያስችለው ቁመና እንዲላበስ ተደርጎ የተሰራ ነው ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ወደ ትግበራ ሲገባ በከተማዋ የሚከሰቱ በርካታ አደጋዎችን ይቀርፋል፡፡ እንዲሁም የት ቦታ ምን አይነት አደጋ እንደተከሰተ በመጠቆም ጉዳት ሳይደርስ አደጋውን ለመቆጣጠር ይረዳል፡፡ ፕሮጀክቱ ከሶስት እስከ አራት ወራት ውስጥ ተጠናቆ አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

# በበዓላት ወቅት ከሚፈጸም ዕርድ የሚሰበሰበው ቆዳና ሌጦ ከ30 በመቶ አይበልጥም

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- በበዓላት ወቅት ከሚፈጸመው የዕርድ ሥነ-ሥርዓት የሚሰበሰበው ቆዳና ሌጦ ከ30 በመቶ እንደማይበልጥ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል አስታወቀ፡፡

የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል የቆዳ ቴክኖሎጂ ዘርፍ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሚሻሞ ዋካሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበዓላት ወቅት ከፍተኛ የእንስሳት እርድ ቢከናወንም ወደፋብሪካዎች የሚገባው ቆዳና ሌጦ አነስተኛ ነው።

የተደራጁ የቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች አለመኖራቸው ለዘርፉ ትልቅ ፈተና ነው ያሉት አቶ ሚሻሞ፤ በኢትዮጵያ በዓመት ሊሰበሰብ ከሚገባው 41 ሚሊዮን የበሬ ቆዳ፣ የበግና የፍየል ሌጦ ውስጥ ከ25 እስከ 30 መቶ ብቻ ለኢንዱስትሪዎች እየቀረበ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በበዓላት ቀናት ከፍተኛ የቆዳ እጥረት አለ ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ በበዓል የሚገኘውን የቆዳ ውጤት በሚገባ ሰብስቦ በከፊል አዘጋጅቶ ማስቀመጥ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ሚሻሞ እንዳመለከቱት፤ ዕርድ የሚፈጽሙ ሰዎች በግንዛቤ ማነስ፣ ቆዳና ሌጦ የሚሸጥበት ዋጋ አነስተኛ ነው በሚልና በቸልተኝነት ቆዳን ለኢንዱስትሪዎች አያስተላልፉም፡፡ በመሆኑም ያለቀለት ቆዳ ለማምረት የበዓላትን ወቅት በሚገባ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት የቆዳና ሌጦ የአቅርቦት ሥርዓት ማሻሻል ላይ በትኩረት ይሠራል ያሉት አቶ ሚሻሞ፤ እንስሳቱ በሕይወት እያሉ ትክክለኛ እንክብካቤ አለማድረግና በተዋሲያን መጎዳት፣ በዕርድ ወቅትና በሚደረጉ ሂደቶች ቆዳው ጥራቱን ስለሚያጣ የቆዳዎች ጥራት ዝቅተኛ ይሆናል ብለዋል።

በምርት ሂደት ወቅት አንድ ቆዳ የክብደቱን 35 በመቶ ጨው ማግኘት አለበት ያሉት አቶ ሚሻሞ፤ ነገር ግን በጨው እጥረት ምክንያት አነስተኛና ደጋግሞ መጠቀም የዘርፉ ፈተናዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በዕርድ ወቅት ጥንቃቄ ባለመኖሩ ቆዳዎች ጥራት የላቸውም ያሉት አቶ ሚሻሞ፤ ቆዳና ሌጦ የሀገር ሀብት መሆኑን አውቀው በዕርድ ወቅት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለቄራዎችና ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዕርድ የሚፈጽሙ ሰዎች ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሰርተፍኬት እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የቆዳ ገበያ እንዲሻሻል የቆዳ ፋብሪካዎች አቅማቸውን ማሳደግ አለባቸው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ካለን የሕዝብ ቁጥር ውስጥ በብዛት ወጣቶች በመሆናቸው የቆዳ ምርቶችን የሚያመርቱ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በማስፋፋት ለሚሊዮኖች የሥራ ዕድል መፍጠር ይገባል ብለዋል፡፡

ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ባለባቸው አካባቢዎች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የሚባክን ሀብትን ወደ ኢኮኖሚ መቀየር ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

በ2016 ዓ.ም አዲስ ዓመት የበሬ ቆዳ ከ250 እስከ እስከ 300 ብር፣ የበግ ቆዳ ከ80 እስከ 90 ብር የፍየል ሌጦ ከ20 እስከ 30 ብር መሰብሰቡን አቶ ሚሻሞ አስታውሰዋል፡፡

# በክልሉ በዓላቱ ትውፊታቸውን ጠብቀው በሰላም እንዲከበሩ ዝግጅት ተደርጓል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮው የመውሊድ፣ የደመራ፤ የመስቀል እና የእሬቻ በዓላት ትውፊታቸው ተጠብቆ በሰላም እንዲከበሩ የሚያስችል የዝግጅት ሥራ መሠራቱን የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትልና የባህል ዘርፍ ኃላፊ አቶ አብረሃም ቡጤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዘንድሮው የመውሊድ፣ የደመራ፤ የመስቀል እና የእሬቻ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ ለማስቻል የተለያዩ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡

በዓላቱ ባህላቸው፣ ወጋቸውና የአከባበር ሥርዓታቸውን ጠብቀው ያለምንም የፀጥታ ስጋት በሰላም ተከብረው እንዲውሉና ባህላቸው ሳይበረዝ ከነ ትውፊታቸው እንዲከበሩ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከአባ ገዳዎችና ሀደ ስንቄዎች እንዲሁም ከማኅበረሰቡ ጋራ በቅርበት እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

ማኅበረሰቡ ወደ አደባባይ በነቂስ ወጥቶ በጋራ የሚያከብራቸው የአደባባይ በዓላት ማለትም የደመራ፣ የመስቀል፣ የእሬቻ፣ የመውሊድና ሌሎች የአደባባይ በዓላት የሀገርና የሕዝብ ሀብቶች ናቸው ያሉት አቶ አብረሀም፤ በዓላቱ ጎልተው እንዲከበሩ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በዓላቱ የማኅበረሰብን አንድነት በማጠናከር ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመው፤ በክልሉ ይበልጥ እንዲጠናከሩና እንዲለሙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በዓላቱ ቱሪዝምን በማሳደግ ሀገሪቱ እያሳየች ያለውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት አጠናክረው የሚያስቀጥሉ ናቸው ያሉት አቶ አብረሃም፤ በዓላቱ ሊጠበቁና ሊያድጉ ይገባል፤ ይህንንም ማኅበረሰቡም ሆነ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራበት ይገባል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በዓላቱ በክልሉ በሚከበሩባቸው አካባቢዎች የፀጥታ ስጋት እንዳይፈጠር ኅብረተሰቡ ኮሚቴ በማዋቀርና ከመንግሥት አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የበዓላት እሴት፤ ባህልና ትሩፋት በሌሎች ሀገራት ባህል ሳይመረዙ በነበራቸው የአከባበር ሥርዓት እንዲከበሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት ተደርጓል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

የአደባባይ በዓላት በስፋትና በድምቀት እንዲከበሩ ቢሮው መጠነ ሰፊ ሥራ ሠርቷል ያሉት አቶ አብረሃም፤ የተሠራውም ሥራ ከበዓላት የአከባብር ሥርዓት ውጪ የሆኑ አስተሳሰቦችና እንቅስቃሴዎች እንዲመክኑና በሰላም እንዲከበሩ ያስችላል ብለዋል፡፡

ክልሉ የአደባባይ በዓላት ባህላቸውን፣ እሴታቸውን፣ ትሩፋታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲከበሩና አከባቢ ማኅበረሰብም በሰላም በዓሉን አክብሮና አምልኮታዊ ሥነሥርዓቱን ፈፅሞ ወደ ቤቱ እንዲመለስ የሚያስችል ሥራ መሠራቱንም አመላክተዋል፡፡



# “የመስቀል ዋና መልዕክቱ ጥላቻን መግደል ነው”

- ዳንኤል ሰይፈሚካኤል የሥነመለኮት መምህር

**ዘላለም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- የመስቀል ዋና መልዕክቱ ጥላቻን መግደል በመሆኑ በዓሉን ለሰው ልጅ ሰላም ክብር እና ፍቅር በማሰብ ልናከብረው ይገባል ሲሉ የሥነመለኮት መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ገለጹ:: የደመራ በዓልም የእኩልነት፣ የሰላም እና የነጻነት በዓል እንደመሆኑ በሕይወት አኗኗርም ሆነ በበዓሉ አከባበር ታሪካዊ አውዱን የሚመጥን መንፈሳዊ ገጽታ መላበስ እንደሚገባ አሳሰበዋል::

መምህር ዳንኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መስቀሉ የአሸናፊነት፣ የነጻነትና የሰላም ምልክት ነው:: ነገረ መስቀሉ ጳውሎስ ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ግን ሕይወት ነው ብሎ የተናገረው መልእክቱ ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን በመስቀል በከፈለው መስዋዕትነት ተለያይተው የነበሩ ሰውና ፈጣሪ አንድ ያደረገበት እንደመሆኑ የአንድነት፣ የመተሳሰብ፣ የመስዋዕትነት፣ የሉአላዊነት እና የሕይወት ምልክት ነው::

በዓሉን ከዋናው መልእክት በተቃራኒ ሆኖ ማክበር አይቻልም:: መስቀል ዋና መልእክቱ ጥላቻን መግደል ነው:: ለሰው ልጅ ሰላም ክብር እና ፍቅር በማሰብ መሆን አለበት:: መስዋዕትነት የተከፈለበትን ትልቁን ነገረ መስቀል በሕይወት ልንኖረው ይገባል ብለዋል መምህር ዳንኤል::

ብዙ ጊዜ ወደአልተፈለገ ነገር የሚመራን ጥላቻና አሉታዊ አመለካከት እንደመሆኑ እነዚህ የሞት ምልክቶች መሆናቸውን ማሳወቅ፣ መገንዘብና መተው እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል::

የደመራ በዓል የሚከበረው፤ የጌታችን፣ የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ተቀብሮ ከቆየበት ቦታ የተገኘበትን ዕለት ምክንያት በማድረግ መሆኑንም መምህር ዳንኤል አስታውሰው፤ በበዓሉ መስቀሉ ነገረ ደህንነትና ትምህርተ ሃይማኖት ጋር ያለውን ግንኙነት በማያያዝ መልእክት ይተላለፍበታል ብለዋል::

የቤተ ክርስቲያን ትልቁ ምልክት ውስጥ የተደረጉ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ታሪካዊ ክስተቶችን መሰረት በማድረግ ይተረካል:: በመሆኑም በዓሉን ‹‹በመስቀሉ ጌታችን በእለተ አርብ መስዋእትነትን ከፍሎ ተሰቅሎ ሞታችንን በሞቱ ሽሮ እኛን ያዳነበትን ምስጢር ገልጠን መስቀሉ የት እንደሄደ፣ ምን እንደሆነ፣ ተቀምጦ የነበረበትን እናነሳለን›› ብለዋል::

አዲስ ዓመት መቀበያ ላይ ከዘመን አቆጣጠር ኡደት ጋር ይገጣጠማል:: አዲሱን ዓመት ከመባረክና ከመቀበል የተፈጥሮ ሂደት ጋር ይያያዛል:: በትውፊቱ አደይ አበባን መስቀሎችን የያዘ በመሆኑ የመስቀል አበባ እንለዋለን:: እነዚህን ሁሉ አጣምሮ ከንጉስ ኢዛና፣ ከንጉስ ገብረመስቀል፣ ከንጉስ ሳሌም ጀምሮ በኢትዮጵያ እንደሚከበርም አስታውሰዋል::

300 ዘመን ክርስቲያኖች ከጌታችን የስቅለትና በሦስተኛው ቀን ወደሰማይ ካረገ በኋላ ክርስትና ሃይማኖት በሮማውያን ዘንድ የነበረበትን ስደት እየተረከን ወደ ነጻነት መስቀሉ ከተገኘበት ታሪክ ጋር የሚገናኘው ቆስጠንዮስ የተባለው የሮም ንጉስ እናት እሌኒ መስቀሉን እንዴት እንዳገኘች ለዛ ምክንያት የሆናትን የፈርኦን መንግሥት ረጅም ዘመን የነበረውን ተጽእኖና መከራ የሃይማኖት ነጻነት የታወጀበት ነበር ሲሉም አብራርተዋል::

ከዚያም የክርስትና ሃይማኖት ከስደት ነጻ የሆነበትን መሰረት በማድረግ በንግስት እሌኒ ከሮም በመነሳት እየሩሳሌም በመሄድ መስቀሉ ብዙ ዘመን ተቀብሮ ስለነበር ለማግኘት የተቀበረበት ቦታ በእጣኑ ጭስ ለማመልከት በሽማግሌዎች ምክር በመያዝ ነው ታሪካዊ ዳራው የሚነገረው፤ ይህ ዓለም አቀፍ ታሪክ ነው ብለዋል::

አንድ ታክ እውነተኛና ተቀባይነት እንዲኖረው ከሚያደርጉት ዋናው ታሪኩ በተፈጠነበት ዘመን ተመሳሳይ በሆኑ ወቅቶች የተደረጉ የጽሁፍ ምስክሮችን መሰረት ማድረግ ነው:: ታሪኩ በነበረበት ዘመን በሕይወት የነበሩ ብዙ የታሪክ ጸሐፍቶች ክስተቱን በአንድ አይነት አገላለጽ አስፍረውታል::

ክርስትና ሃይማኖት ከሐዋርያት ተቀብለው ያቆዩ ተቋማት ይተርኩታል:: ሲተርኩ በታሪክ ብቻ ሳይሆን በቅዳሴ፣ በሥርዓተ አምልኮ፣ በመንፈሳዊ ትውፊትና በሌሎቹ የአምልኮ ሥርዓቶች ይከበራል:: በሮም፣ በሶሪያ፣ በአርመን፣ በግብጽ፣ በሁሉም የኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትና ጥንታውያን በሚባሉ አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ታሪኩ ይታወሳል::

በሁሉም የኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሚታወስበት ምክንያት ከደህንነት ጋር ስለሚያያዝ የክርስትና ሃይማኖት ነጻነት የተገኘበት ዘመን ይተርካል::

በክርስቲያናት ዘንድ መስቀሉ የመስዋዕትነት፣ ጌታችን ለሰው ልጅ ስለከፈለው መስዋዕትነት በመተረክ ህይወትን እስከመስጠት ድረስ የተከፈለ የመስዋዕትነትና የፍቅር ስጦታን በማሰብ ነው:: የደህንነት፣ የሰላም፣ የእርቅ እና የአሸናፊነት ምልክት ነው::

በመስቀሉ የተደረጉትን መሰረት አድርገው ክርስቲያኖች በየዓመቱ ይዘክሩታል:: በኢትዮጵያም ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ክርስትና የነበረ ቢሆንም፤ በዋናነት እውቅና አግኝቶ ጥንታዊ እሴትን ጠብቆ በዓሉ በአደባባይ መከበር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው:: ይህ ጊዜም መስቀሉ ከተገኘበት የ10 እና የ15 ዓመት ልዩነቶች አልነበሩም::

ስማችን እንኳን ገብረመስቀል፣ ወልደመስቀል፣ ኃይለመስቀል... በሚል ከጥንት ጀምሮ ይሰየም ነበር:: በስድስተኛውና በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ገብረመስቀል የሚባል ንጉስ ነበረ:: ከማኅበራዊ ሕይወት ጋር የተሳሰረ መሆኑንም የሥነመለኮት መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል አመልክተዋል::

# “ምዕመኑ የደመራ በዓልን ሲያከብር አንድነቱንና አብሮነቱን በሚያጠናክር መልኩ ሲሆን ይገባል”

- የሃይማኖት አባቶች

**ቃልኪዳን አሳዬ**



ሊቀ ትጉሀን ተድላ ሰንበት



መምህር መዝገበቃል ገብረሕይወት

አዲስ አበባ፡- ምዕመኑ የደመራ በዓልን ሲያከብር አንድነቱንና አብሮነቱን በሚያጠናክር መልኩ መሆን አለበት ሲሉ የሃይማኖት አባቶች አሳሰቡ።

የመስቀል ደመራ በዓልን አስመልክተው ከኢፕድ ጋር ቆይታ ያደረጉት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መምህር የሆኑት ሊቀ ትጉሀን ተድላ ሰንበት እንደገለጹት፤ በዓሉን የሚያከብር ሁሉ መረዳዳትንና አንድነትን ስንቁ ሊያደርግ ይገባል።

በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የመስቀል በዓል እየሱስ ክርስቶስ በሞቱ አንድነትን ያጸናበት በዓል በመሆኑ ዕለቱ በሰፊው ይከበራል፤ በመሆኑም በዓሉን አብሮነትንና ፍቅር በሚገልጽ መልኩ ማክበር ይገባል ብለዋል፡፡

ምዕመኑ መስቀል የፍቅርና የአንድነት ምልክት መሆኑን በመረዳት መረዳዳትንና አብሮነቱን በሚያጠናክር መልኩ በዓሉን ሊያከበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

በመስቀል ደመራ በዓል በርካታ ሕዝብ በአንድነት ወጥቶ በአደባባይ የሚታደምበት በዓል ነው ያሉት ሊቀ ትጉሀን ተድላ፤ በዓሉ በሚደምቅባቸው ስፍራዎች ሁሉ መልካም ስነ-ምግባርን በተከተለና በመተሳሰብ ስሜት ማክበር እንደሚገባ አመላክተዋል።

እንደ ሊቀ ትጉሀን ተድላ ገለጻ፤ የመስቀል አስተምህሮ ሰላምን የሚሰብክ በመሆኑ ምዕመናን ከጥላቻና ከመለያየት ርቀው ፈጣሪ ያደረገላቸውንና የከፈለላቸውን ዋጋ በማሰብ በጋራ ሊያከብሩት ይገባል።

በዓላት ፍቅር የገባቸው ሰዎች የሚያከብሩት እንጂ ጥላቻ ያላቸው ሰዎች አጀንዳ ማስፈጸሚያ አይደሉም ያሉት ሊቀ ትጉሀን ተድላ፤ ምዕመኑ የመስቀል ደመራ በዓልን ለማክበር ሲነሳ ፍቅርና አብሮነቱን ሊያጸኑ የሚችል ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት ጠቁመዋል።

የእየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀሉ በኢትዮጵያ ግሸን ደብረ ከርቤ እንደሚገኝ ያስታወሱት ሊቀ ትጉሀን ተድላ፤ ምዕመኑ ታሪካዊ ቦታዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በመጠንቀቅና ሕዝብን ከሚያሸብሩ ድርጊቶች በመራቅ በዓሉን ሊያከብር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በዋግኽምራ ሀገረስብከት ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ የጉባዔ ቤት መምህር የሆኑት መዝገበ ቃል ገብረሕይወት በበኩላቸው፤ የመስቀል በዓል ለሀገራችንም ሆነ ለዓለም ሕዝም ትልቅ ፋይዳ ያለው የቱሪዝም ሀብት በመሆኑ በዓሉን ስናከብር እምነቱ የሚፈቅደውን በጎ ተግባር በማከናወን ሊሆን ይገባል ብለዋል።

መምህር መዝገበ ቃል እንደገለጹት፤ መስቀል እግዚአብሔር ሰውን ያዳነበት፣ ሰውና እግዚአብሔር የታረቁበት እንደመሆኑ መጠን በዓሉ ሰላምና እርቅ የሚሰበክበትና በሀገሪቱ ላይ እየታየ ያለው ችግር የሚቀረፍበት እንዲሆን መስራት ይገባል።

ሕዝበ ክርስትያኑ እንደሀገር አንድነትን ለማጽናት ለሚደረገው ጥረት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ያሉት መምህር መዝገበቃል፤ በዓሉ መንፈሳዊ በዓል በመሆኑ የእምነቱን አስተምህሮ በተከተለ መንገድ ከዳንኪራና ከግጭት በራቀ መልኩ ማክበር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በዓሉ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ በየቤተ እምነቱ ሰላምን የሚሰብኩ ዕውነተኛ ትምህርቶች ያስፈልጋሉ። ኅብረተሰቡም ቤተክርስትያን ከምትከተለው ሥርዓት ውጪ ባለመሆን ለቃሏ ተገዥና ሰላምን የሚያሰፍን መሆን አለበት ብለዋል።

የሃማኖት አባቶቹ የመስቀል ደመራ በዓል ለመላው የኢትዮጵያ ምዕመናን የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነትና የአብሮነት በዓል እንዲሆንም ተመኝተዋል።

# በዓላቱ በሰላም እንዲጠናቀቁ ኅብረተሰቡ የፀጥታ ሥራን በማገዝ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የደመራ፣ የመስቀል፣የመውሊድና የኢሬቻ በዓላት በሰላም እንዲጠናቀቁ ኅብረተሰቡ የጸጥታ ሥራን በማገዝ ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት የአዲስ አበባ ፖሊስ ገለጸ፡፡ በመዲናዋ በዓላቱ በሰላም እንዲከበሩ የፀጥታ ግብረ ኃይሉ ዝግጅቱን ማጠናቀቁም ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ፖሊስ በዓላት በሰላም ተከብረው እንዲጠናቀቁ ሰፊ ዝግጅት አድርጓል፡፡ የመስቀል፣ የመውሊድና የኢሬቻ በዓላት በሰላም እንዲጠናቀቁ የፀጥታ ግብረ ኃይሉ ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡ ኅብረተሰቡም በዓላቱ በሰላም እንዲከበሩ የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት፡፡

የፖሊስ ሥራ መሰረቱ የኅብረተሰቡ መረጃ ነው ያሉት ምክትል ኮማንደሩ፤ በየአካባቢው ፖሊስ ለሚሰራው የፀጥታ ሥራ ኅብረተሰቡ ተባባሪ መሆን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

የመስቀል ደመራ በሚደመርበት ሰዓት ላይ በዓሉን የሚያውኩ ግጭት ቀስቃሽ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን የገለጹት ምክትል ኮማንደሩ፤ በዓሉን የማይመጥኑ ቁሳቁሶችንም ይዞ መምጣት እንደማይቻል አመልክተዋል፡፡ ለጸጥታ አካላት የፍተሻ ሥራም ኅብረተሰቡ ተባባሪ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

ሃይማኖታዊ ይዘት የሌለው ፣ አንዱን ብሔር ከአንዱ የሚያጋጭና አንዱን ዝቅ ሌላውን ከፍ የሚያደርግ ተግባር ፈጽሞ የተከለከለ ነው ያሉት ምክትል ኮማንደር ማርቆስ፤ አሽከርካሪዎችም ወደ መስቀል አደባባይ የሚያመጡ መንገዶች በሙሉ በበዓላቱ ቀናት ዝግ ስለሚሆኑ አማራጭ መንገዶችን መጠቀም እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል፡፡

በየመንደሩ በጣም በርካታ የሆነ ደመራ እንደሚደመር አንስተው፤ ኅብረተሰቡ ደመራውን ከመደመሩ በፊት የኤሌክትሪክና ሌሎች አደጋዎችን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች አከባቢው ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል፡፡ ርችት መተኮስ እንደማይቻልም ነው የተናገሩት፡፡

በመዲናዋ በፀጥታ ሥራ በተደረገው ጥሩ ዝግጅት አዲስ ዓመት በሰላም መጠናቀቁን አስታውሰው፤ የነበሩ ደካማና ጠንካራ ጎኖች ተለይተው ለመስቀል በዓል የበለጠ ዝግጅት እንደተደረገ ገልጸዋል፡፡

መላው የፖሊስ አባላትና አመራሮች ከአዲስ ዓመት ጀምሮ በበዓላት ሥራ ላይ መሆናቸውን የተናገሩት ምክትል ኮማንደር ማርቆስ፤ ወንጀል መከላከል እና የኢ.ሬቻንም በዓል ሰላማዊ ለማድረግ ዝግጅቶች ተጠናቀው ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል፡፡ በመስቀል በዓል የሚታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖች ተለይተው ለኢሬቻ በዓል ዝግጅቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሚደረጉም አመልክተዋል፡፡

በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች በከተማዋ እንደሚገኙ እንዲሁም በዓሉን ለማክበር ቱሪስቶች እንደሚመጡ ጠቁመው፤ የጋራ የሆኑት በዓላት ሰላማዊ ሆነው እንዲከበሩ ሁሉም ሰው ኃላፊነቱን በተገቢው መልኩ እንዲወጣም ጠይቀዋል፡፡

ለሰላምና ደህንነት አጠራጣሪ የሆኑ ነገሮች በሚያጋጥሙ ወቅት ለፖሊስ በአፋጣኝ መረጃ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ በአዲስ አበባ ፖሊስ የመረጃ ስልክ ቁጥሮች 011-1-11-01-11 እና 991 በመደወል መረጃ መስጠት እንደሚቻልም አመልክተዋል፡፡

# የመውሊድና የደመራ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ጽዳት ተካሄደ

**ቃልኪዳን አሳዬና አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የመውሊድና የመስቀል ደመራና በዓላትን በማስመልከት በታላቁ አንዋር መስጂድና በመስቀል አደባባይ ከተለያዩ እምነቶች የተወጣጡ የሃይማኖት አባቶችና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት የጽዳት መርሀ ግብር ተካሂዷል፡፡

በመስቀል አደባባይ የተገኙት በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጥራቱ በየነ እንደገለጹት፤ የጽዳት መርሀ ግብሩ ዓላማ በዓሉን ለሚያከብሩ ወገኖች አብሮነትንና ፍቅርን ለማሳየት ነው።

በከተማዋ የሚከበሩ የመውሊድና የደመራ በዓላት በአንድ ቀን መዋላቸው ታሪካዊ ሁነት በመሆኑ፤ በአንዋር መስጊድና በመስቀል አደባባይ ጽዳት መካሄዱ አብሮነትና ወንድማማችነታችንን ያጠነክራሉ ብለዋል፡፡

በዓላቱ ተጀምረው እስከሚጠናቀቁ ፍፁም ሃይማኖታዊ ሥርዓትን በተከተለ መልኩ ማክበር ይገባል ያሉት አቶ ጥራቱ፤ በዓላቱ ትውፊታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የጠቅላይ ቤተክህነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሊቀ አዕላፍ ቀሲስ በላይ መኮንን በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የጽዳት ሥነሥርዓቱ ከተለያዩ ዕምነት ከተውጣጡ ዜጎች ጋር መደረጉ አንድነትን ያጠናክራል።

ከመስቀል የምንማረው ሰዎች ከራሳቸው አልፎ ለሌሎች በመኖር ለሀገር ለወገን ዋጋ መክፈል እንዳለባቸው ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያዊያን አብሮ የመኖርና የመቻቻል ባህልን ማጠናከር ይገባል ያሉት ቀሲስ በላይ፤ የመስቀል በዓል የሁሉም ሀብትና ቅርስ በመሆኑ በዓሉ በሰላም እንዲከበር የሁሉም ዜጋ አስተዋጽኦ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በታላቁ አንዋር መስጂድ የጽዳት መርሀ ግብር ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ምክትል ዳይሬክተር አቶ ሙላቱ ተገኝ እንደገለጹት፤ የመውሊድ በዓል የሚከበርበትን ስፍራ ለማጽዳት ሁሉም በአንድነት መሰባሰቡ የጋራ እሴቶችን በመጠበቅ በዓሉን በድምቀት ለማክበር ይረዳል።

ትብብርና አብሮነት እሴቶቻችን ናቸው ያሉት አቶ ሙላቱ፤ በዓሉን በጋራ በማክበር አንድነትን ማጠናከር እንደሚገባም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል ሼህ አብዱልሂሚድ አሕመድ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ሕዝበ ሙስሊሙ የነብዩ መሐመድን (ሶ.ዐ.ወ) ልደት የሚያከብረው የእሳቸውን የደግነት ሥራዎች ተግባራዊ ለማድረግና ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ነው፡፡

በአብሮነት ቆሻሻን ማጽዳት አንዱ እምነት ለሌላኛው እምነት ክብር የመስጠቱ ማሳያ ነው ያሉት ሼህ አብዱልሂሚድ፤ አብሮነትና የእምነት መቻቻል ለምንፈልገው የሰላም መረጋገጥ አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡

ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር የተቸገሩትን በመርዳት፣ የታመሙትን በመጎብኘትና የሕግ ታራሚዎችን በመጠየቅ ሊሆን እንደሚገባም መልዕክት አስተላልፈዋል።

በጽዳት ዘመቻ መርሀ - ግብሮቹ ላይ የተለያዩ የሃይማኖት አባቶች፣ የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ሥራ ኃላፊዎች፣ የክፍለ ከተማ አመራሮችን ፣ የፅዳት ሠራተኞች ጨምሮ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶችና የተለያዩ የመዲናዋ ነዋሪዎች ተሳትፈዋል፡፡

# የበዓል ገበያውን ለማረጋጋት ከኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ጋር በትብብር እየተሠራ ነው

## - ለበዓላቱ የሸንኩርት ምርት በስፋት ለማስገባት ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየሠራ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የከተማውን የበዓል ገበያ ለማረጋጋት ከክልል ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ጋር በትብብር እየሠራ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ አስታወቀ። ለመስቀልና መውሊድ በዓላት የሽንኩርት ምርት በስፋት ለማስባት ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየሠራ መሆኑን ኤጀንሲው ገልጿል።

በኤጀንሲው የግብይትና ማደራጀ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብተየስ ዲሮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የከተማውን የገበያ ሁኔታ ለማረጋጋት ከክልል ኅብረት ሥራ ዩኒኖች ጋር በጋራ እየተሠራ ነው።

ምክትል ኃላፊው እንደተናገሩት፤ የዋጋ ግሽበቱን ለማረጋጋት ከኦሮሚያ ኅብረት ስራ ዩኒየን ምርት እንዲገባ እየተደረገ ሲሆን፤ ከአማራ፤ ከአፋርና አዳዲስ ክልሎችን ጨምሮ ከተለያዩ ክልሎች ምርቶች ወደመዲናዋ እንዲገቡ ትስስር በመፍጠር እየተሠራ ነው ብለዋል።

ምርት ከአርሶ አደሩ በቀጥታ ገዝቶ ለማስገባትና ለኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱ እንዲቀርብ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

የአቅርቦት ስራው ምርት በማከፋፈል ሂደት ሕገወጥ ደላሎች ሲገቡ የሚፈጠረውን የዋጋ ጭማሪ ይቀንሳል ያሉት አቶ ሀብተየስ፤ በኅብረት ሥራ ኤጀንሲው በኩል የሚገቡ ምርቶች የጫኝና አውራጅ ዋጋ ብቻ ተጨምሮባቸው በተመጣጣኝ ለሸማቹ እንዲቀርቡ እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በዓልን ተከትሎ የምርት እጥረት እንዳይኖር በስፋት ምርቶች መግባታቸውን እና በመግባት ላይ እንደሚገኙ ያነሱት ምክትል ኃላፊው፤ የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የእንስሳት ተዋጽኦዎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

አቶ ሀብተየስ እንዳስታወቁት፤ የጤፍ ምርት በተመለከተ ከዚህ በፊት መጋዘን ካለው በተጨማሪ በዓልን አስመልክቶ ከ10 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ወደ አዲስ አበባ ገብቷል።

በመጋዘን የሚገኘውን 30 ሺህ ኩንታል ጤፍ እንዲሁም ከአንድ ሺህ ኩንታል በላይ የበቆሎ ዱቄት ለኅብረተሰቡ



**አቶ ሀብተየስ ዲሮ**

እየቀረበ መሆኑን ገልጸዋል።

ከኢንዱስትሪ ምርቶች ጋር ተያይዞ ዘይትን ጨምሮ የተለያዩ ምርቶች መግባታቸውን ተናግረው፤ ከአንድ ሺህ 800 በላይ ኩንታል ማካሮኒ በቅርቡ እንደገባ ተናግረዋል።

አቶ ሀብተየስ አያይዘው እንደገለጹት፤ ሰሞኑን ባጋጠመው ዝናብ ምክንያት ወደ ማሳ እንደልብ መግባት ባለመቻሉ ሽንኩርት በስፋት ማቅረብ አልተቻለም።

በመሆኑም የአቅርቦት እጥረቱን ተከትሎ የዋጋ ጭማሪ መከሰቱን አንስተው፤ በተለይ የሽንኩርት ምርት ዋጋ መናር ማጋጠሙን አስረድተዋል።

የኅብረት ሥራ ኤጀንሲው ችግሩን ለመቅረፍ ግብረኃይል አቋቁሞ በመሥራት ላይ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

ለበዓላቱ የሽንኩርት የምርት እጥረት እንዳይከሰት ግብረ ኃይል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቁጥጥር እያደረገ ምርት በብዛት እንዲገባ እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ያጋጠመውን ችግር ለመቅረፍ እስከ ሱማሌ ክልል ድረስ በመሄድ ምርት እንዲገባ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ያሉት አቶ ሀብተየስ፤ ኅብረተሰቡ ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸመት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የገበያ ማዕከላት እንደአማራጭ መውሰድ እንደሚችል ገልጸዋል።

# የመስቀል ደመራና የመውሊድ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መልካም ምኞቱን አስተላልፏል።

ሁለቱም በዓላት ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸው በሚፈቅደው መሠረት በሰላም ተጀምረው በሰላም እንዲጠናቀቁ ከሃይማኖት አባቶች እና ከሰላም ወዳዱ ኅብረተሰብ ጋር በመተባበር በቂ ዝግጅት አድርጎ ወደ ተግባር መግባቱንም የጋራ ግብረ-ኃይሉ ገልጿል።

በሃይማኖት ሽፋን እኩይ የፖለቲካ አጀንዳዎቻቸውን ለማራመድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተገቢ እንዳልሆኑ ሁሉም ሊገነዘብ እንደሚገባ አመላክቷል።

ከበዓላቱ አከባበር ሥነ-ሥርዓት ውጪ ግጭትና ሁከት ቀስቃሽ መልዕክቶችን በባነር፣ በአልባሳት እንዲሁም እንደ ርችት የመሳሰሉ ተቀጣጣይ ነገሮችን፣ ስለታማና የጦር መሳሪያ በማንኛውም ሁኔታ በዓላቱ ወደ ሚከበሩባቸው ቦታዎች ይዞ መግባት በጥብቅ መከልከሉን አስታውቋል።

ክልከላውን ተላልፈው የበዓላቱን ድባብ ለማደብዘዝ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይም ጥብቅ ሕጋዊ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ከወዲሁ ገልጿል።

በዓላቱ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በሰላም ተጀምረው በሰላም እንዲጠናቀቁ የጋራ ግብረ-ኃይሉ በቂ ዝግጅት አድርጓል ሲል የገለጸው የጋራ ግብረኃይሉ ኅብረተሰቡም ለፀጥታ ኃይሉ አጋዥና ተባባሪ በመሆን የድርሻውን እንዲወጣ አሳስቧል።

በበዓላቱ ድባብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚደረግ ማንኛውም ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴ የሕዝቡን ሰላምና ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ የሃይማኖት አባቶች፣ በዓሉን በኮሚቴነት የምታስተባብሩና የሚመሩ አካላት፣ ሕዝበ ክርስቲያንና ሕዝበ ሙስሊሙ ከፀጥታ አካላት የሚሰጠውን መመሪያ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዓላቱ በሰላም ተጀምረው በሰላም እንዲጠናቀቁ ትብብርና ድጋፍ እንዲያደርጉ የጋራ ግብረ-ኃይሉ ጥሪውን አቅርቧል።

ኅብረተሰቡ በዓላቱን የሚያውኩ የተለዩ እንቅስቃሴዎችን በአቅራቢያ ለሚገኙ የፀጥታ አካላት በመጠቆም ሰላምና ደኅንነትን የማስከበር እንቅስቃሴ ላይ አጋርነቱን አጠናክሮ እንዲቀጥልም የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል በመግለጫው አስታውቋል።

# ‘ማርያምን’ እና ‘ወላሂ’ እኩል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ቀን ይውላሉ:: በእንደዚህ አይነት ቀን ሁለቱም ቤት ድግስ አለ:: ሁለቱም ተደሳች ናቸው:: የእምነቱ ተከታዮች ተጎራብቶ ከመኖር ያለፈ ታሪክ ባለቤት ናቸው:: ተግባብተው ተጋብተው ይኖራሉ:: ይህ ለሕዝቦቹ አዲስ አይደለም::

በዛሬን መሳይ የሁለቱም በዓላትን አሳላፊ ቀን ላይ አንድ ቤተሰብን ማወቅ ያሻል:: መስቀልንም መውሊድንም ያከብራሉ:: ሁለቱም የአንደኛው ጎናቸው ነው:: ያለ አንዱ ሌላኛቸው ምንም ናቸው:: ይህ ቤተሰብ የአቶ ከድር መሀመድና የባለቤቱ ነው:: ቤተሰቡ ለሁለቱ እምነቶች ተከባብሮ ኗሪነት ህያው ምስክሮች ናቸው:: የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከዚህ ቤተሰብ አባል ጋር ቆይታ አድርጓል::

ልጃቸው ሩሀማ ከድር ትባላለች:: እናቷ ወይዘሮ አሰፋሽ አስናቀ ይባላሉ:: አባቷ አቶ ከድር መሐመድ ናቸው:: እናት የኦርቶዶክስ ክርስቲያን እምነትን ይከተላሉ:: አባት ደግሞ እስልምናን:: ከኢትዮጵያ ጅቡቲ ተመላልሰው የሚሰሩ ሹፌር ናቸው:: ወላጆቿ በትዳር ላይ ሆነው 33 ክረምቶች ወግገዋል::

ሩሃማ በሶስት እህቶቿ በታጀበው ቤተሰብ ውስጥ የመጨረሻ ልጅ ናት:: ተከባብሮ ተዋዶ የሚኖርበት ቤት ውስጥ አደገች:: በነ ሩሀማ ጎጆ ሁለቱንም በዓል እያከበሩ ነው የሚታደገው:: ለሩሃማና ሶስት እህቶቿ ልጅነታቸው በደስታ ያለፈ ነው:: ባህሉን የመታደም እድል ገጥሟቸዋል:: የአባት ሹፌርነት አንዳንዴ በዓልን ቤታቸው እንዳያሳልፉ ያደርጋቸዋል:: አቶ ከድር የሌሉ ጊዜ ልጆች በመከፋት ያሳልፋሉ::

አቶ ከድር የቤቱ አድባር ናቸው:: በረሀ ለበረሀ ተንከራተው ልጆቻቸውን አሳድገዋል:: ሩሀማ ስለ አባቷ ስታወራ እምባ ከአይኗ ይቀዳል:: እናቷ የእምነቷን በዓላት ሲያከብሩ የባለቤታቸውንም አይዘነጉም::

ለትንሿ ሩሀማ ልጅነቷ ከባድ ጊዜም ነበር:: አባቷ ቤት በሚሆኑበት ወቅት ቁርዓን ትቀራለች:: መስጊድም ይወስዷት ነበር:: ለበዓላት ስቴዲየም ሄዳ ትሰግዳለች:: የእናቷ እናት አያቷ ደግሞ አባቷ ሳይኖሩ የምትሄድባቸው ናቸው:: ያኔ ቤተክርስቲያን ትሄዳለች:: የክርስቲያን አማኞችን ሃይማኖታዊ ተግባራት ትከውናለች:: ትንሽ ነፍሷ መሀል ቤት ትጨናነቅ ነበር:: ማንን ተከትዬ ላስደስት በሚል ሃሳብ:: ካደገች በኋላ ግን የራሷን እምነት ወሰነች:: ቢሆንም ለሌላው እምነት ያላት ክብር አልቀነሰም::

ራሷን ችላ ከቤት ከወጣች በኋላም አባቷን አልረሳችም:: አባቷን ለረመዳን ፆም እሷ ጋር እንዲያሳልፉ ማድረግ ቻለች:: ይህን ለተከታታይ ስድስት ዓመታት ከወነች:: በአባቷ የምትመረቅ ልጅ ናት:: በህይወቷ ለገጠሟት መልካም ነገሮች ሁሉ አመስጋኝ ናት:: የአባቴ ዱአ ነው መልካም የሆነልኝ ባይ ናት::

ሩሀማ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ መወለድ ከብዙ በጎ ነገሮች አስተዋውቆኛል ትላለች:: የሰውን እውነትና እምነት ማክበርና ከነማንነቱ የመቀበልን ጥበብ በአኗኗሬ ተምሬያለሁ ባይ ናት:: ቤተሰቦቿን እያዩ መኖር በፍቅር ማመንና ሰውን ማክበርን አስተምሯታል::

በነሱ ቤት ማርያምን የሚሉት መሃላ ከወላሂ እኩል ይታመናል:: አንዱ የሌላኛውን ሳይጥል የራሱን ያከብራል:: በዚህ ህይወት ውስጥ የሁሉንም እውነት ለመረዳት መታተርን ከቤቶቿ ተምራለች:: ከእናቷም ከአባቷም አፍ የማይታጣ ቃል አለ:: ሩሀማ የሚል:: ሲደሰቱም ተናደው ሲምሉም በእርሷ ነው:: በተለይ አባቷ በቀን ስሟን ጠርተው አይሰለቹም::

ከድሬ ብላ ነው አባቷን የምትጠራው:: ለቤተሰቡ ምሰሶና ዋልታ መሆናቸውን ትመሰክራለች:: የአባት አቶ ከድር የዋህነት የእናቷ ብርታት ጎጇቸውን በመልካም መቀለሱን ልጃቸው ትናገራለች:: በከፋ ቀን ያበረታቸው አብሮ መሆን ነው:: በተካበደ ወቅት የበረቱት በፍቅር ሀያልነት ነው:: ጎራ ለይቶ ለሚከፉ መልዕክት አስተላልፋለች:: አትለያዩ አንዳችን ያለሌላችን ባዶ ነን የሚል::

# “የመውሊድ በዓልን ስናከብር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልካም ነገሮችን ለማስተዋወቅ፣ መጥፎ ተግባራትን ሊቃወሙ የተሰጡ መሆናቸውን አንስተው፤ የሳቸውን አስተምሮ የሚከተል ሁሉ የእርሳቸውን ፈለግ የሚከተል፤ በጎ ነገሮች ተጓድለው ሲገኙ ወገኖችን ለማስተማርና ለመመለስ የሚደክም መሆኑን አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት፤ መውሊደል ነቢ በሚከበርበት ዕለት፣ ሙስሊሞች መስጂድ ሄደው በጋራ ጸሎት ያድርጋሉ፡፡ የታላቁን ነቢይ ሥራዎች፣ አስተምህሮቶች ይዘክራሉ፡፡ ነቢዩ በህይወት ሳሉ የነበራቸውን፣ ትህትና፣ ደግነት፣ ይቅር ባይነት ያስታውሳሉ፡፡

ከመስጂድ ከወጡም በኋላ፣ ያላቸው ከሌላቸው ጋር በመካፈል፣ ለወገኖቻቸው ሁሉ ትሁት በመሆን፣ የበደላቸውን ይቅር በማለት፣ እንደ ዲናቸው መሪ፣ ትህትናን፣ ደግነትን እና ይቅር ባይነትን በተግባር ይፈጽማሉ ብለዋል፡፡

ይህን ታላቁን መውሊድ ስናከብር ለሌሎች እምነት ተከታዮች፣ ወንዱ ለሴቱ፣ ትንሹ ለትልቁ፣ በሀገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ፣ የትም ላለው ኢትዮጵያዊ፣ ሁሉም ለሁሉም ትሁት ይሁን! ደግ ይሁን! በደልም ሲኖር፣ ይቅር ባይነት ይኑር! ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መውሊድ ፤ የሰላምና የአብሮነት በዓል!

መውሊድ በእስልምና የዘመን አቆጣጠር ዘመነ ሂጅራ ራቢአል አወል የተሰኘው ሦስተኛው ወር በገባ በ12ኛ ቀን በየዓመቱ ይከበራል። የቃሉ ምንጭ አረብኛ ሲሆን ትርጉሙም የመወለጃ ቦታ ወይም እለት ማለት ነው።

የመውሊድ በዓል ነብዩ መሐመድ የተወለዱበትን ቀን ለመዘከር በሙስሊሞች ዘንድ የሚከበር በዓል ነው። የመውሊድ በዓል የነቢዩ መሐመድ መልካም ተግባራትን የህይወት መርህ በመከተል ይከበራል። በመውሊድ በዓል ሰላም፣ ፍትሕ፣ በጎነትና አንድነት የመሳሰሉ ነብያዊ ባህርያት ጎልተው የሚወጡበትና ሰዎችም የነብዩ መሐመድን ፈለግ በመከተል የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት ቀን ነው።

ነብዩ መሐመድ በምድር ላይ ሳሉ ሰላም ፍቅርና አንድነትን በማስተማር አርዓያ የነበሩ ነብይ ነበሩ። የነብዩ መሐመድ መልካም ፀባያትም በመላው ዓለም እንዲሰርጽና ሰዎችም ፈለጋቸውን ተከትለው መልካም ተግባራትን እንዲያከናውኑ የመውሊድ በዓል በመላው ዓለም በድምቀት ይከበራል።

የመውሊድ በዓል በኢትዮጵያ መከበር ከጀመር በርካታ ዘመናትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከሌሎች የእምነት ተከታዮች ጋር በጋራ በመሆን በዓሉን ሲያከብሩ ኖረዋል። በበዓሉ ዕለት ሙስሊሞች ክርስቲያን ጎረቤቶቻቸውን በመጥራት እና ማዕድ በመቋረስ በዓሉን በድምቀት ያሳልፋሉ። ስለሀገራቸው ሰላምና አንድነት ይጸልያሉ፤ አብሮነታቸውንም ያጠናክራሉ።

መውሊድ የአብሮነት በዓል ነው። በመውሊድ በዓል ወዳጅ ዘመድ ተሰባስቦ በዓሉን በጋራ ያሳልፋል፤ አብሮነት ይደምቃል። ከዚህ በሻገር ግን ከጥንት በኢትዮጵያ ያለው የመውሊድ አከባበር ለየት የሚልባቸው እሴቶች አሉት። ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ እምነቶችን በፀጋ የተቀበለችና የተለያዩ እምነት ተከታዮችም ተከባብረው የሚኖሩባት የተለየች ሀገር ነች። መውሊድን በመሳሰሉ የበዓል ወቅት ደግሞ በክርስትና በዓላት እንደሚደረገው ሁሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ ጎረቤቶችን በመጥራት በዓሉን በጋራ ማሳለፍ የተለመደ ነው። ይህ አንዱ ኢትዮጵያዊ ዕሴት ሲሆን፤ ለዘመናትም ሲወርድ ሲዋረድ ዛሬ ላይ የደረሰ ድንቅ መገለጫችን ነው።

ነብዩ መሐመድ በእስልምና ሃይማኖት በነበራቸው አስተምህሮት የሰው ልጆች ያለ ዘርና ሃይማኖት ልዩነት የምድር ፍጡራን ሁሉ እኩል መሆናቸውን ሲያስተምሩ የቆዩ በመሆኑ ዛሬ በዘር፣ በጎሳና በሃይማኖት ልዩነት እየተናጠች ለምትገኘው ሀገራችን የነብዩ አስተምህሮት ከፍተኛ ትምህርት ይሰጣል። ሕዝበ ሙስሊሙም ልዩነትን፤ መገፋፋትና መወቃቀስን በማስወገድ ለሀገሩ አንድነትና ሰላም የሚሰራበት ወሳኝ ወቅት ላይ እንደሚገኝ መረዳት አለበት።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት አንዱ የበዓሉ ዕሴት ነው። የእስልምና እምነት ድሆችን ማብላትና ማጠጣት እንዲሁም በዓላትን እኩል በደስታ እንዲያሳልፉ በአማኞች ላይ ግዴታ ጥሎባቸዋል። ከእነዚህ ትዕዛዞች አንዱ ያጡና የተቸገሩ ወገኖችን መርዳትና መደገፍ አንዱና ዋነኛው ነው።

የእምነቱ ተከታዮች በዓላትን ራሳቸው ብቻ ተደስተው እንዲያሳልፉ አይፈቀድላቸውም። ይልቁንም በዓላት ድምቀት የሚኖራቸውና በፈጣሪም ዘንድ ተቀባይነትን የሚያጎናጽፉት ከተቸገሩ ወገኖች ጋር አብሮ ማሳለፍ ሲቻል ነው። ስለዚህም ሙስሊሞች የመውሊድ በዓልን ሲከብሩ ለተቸገሩ ወገኖች ማዕድ ከማጋራት ጀምሮ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ሊሆን ይገባል።

በአጠቃላይ መውሊድ የመረዳዳት በዓል በመሆኑ ከዚህ በሻገር እንደሀገር ትልቅ ፋይዳ ያለው በዓል ነው። በተለይም በአሁኑ ወቅት በጸጥታ ችግር ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉና የተሰደዱ በርካታ ወገኖች አሉ። ከዚሁ ባሻገር በድርቅ የተጎዱና በተለይ በተለያየ መንገድ ጉዳት ደርሶባቸው ያላገገሙ ወገኖች በችግር ውስጥ ስለሚገኙ እነዚህን ወገኖች መደገፍና ተባብሮ ወደ ቀድሞ ህይወታቸው መመለስ አንዱ በመውሊድ ወቅት የሚከወን ተግባር ሊሆን ይገባል።

በአጠቃላይ ሕዝበ ሙስሊሙ 1498ኛውን የመውሊድ በዓል ሲያከብር የነብዩ መሐመድን መልካም ስብዕናና አስተምህሮቶችን በመውሰድ የሀገሪቷን ሰላምና የሕዝቦቿን አንድነት ለማጠናከር መስራት ይጠበቅበታል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የሁላችንም በዓል፤ የሁላችንም ድምቀት

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ከመስከረም እስከ ነሐሴ በሚዘልቀው አስራ ሁለቱ ወራት በእያንዳንዱ ወራት ውስጥ 30 ቀናትን ቆጥረን ዓመት ሞላው ብለን ሳናበቃ እንደገና በእኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ የተለየች አቆጣጠር ጳጉሜን አምስት ወይንም ስድስት ቀን አክልን ይኸው አንድ ዓመት ደፈነ ብለን አዲስ ዓመትን አከበርን።ቡሄ ካለፈ፤ ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ብለን ዝናብ ባያቋርጥም መስከረምን ከክረምቱ ነጥለን ይኸው አንድ ብለን ጀመርን።

በክረምት ዝናብ የጨቀየው መሬት ውሃውን ከከርሱ አምቆ ይዞ፤ መሬቱም ጠገግ ብሎ አዲስ የማለዳ ጀንበር ፈንጥቃ በአበባዮሽ ሙዚቃ ደምቀን፤ አደይ አበባ ታቅፈን እንኳን አደረሳችሁ ተባብለን እነሆ በመልካም ምኞት፣ በተስፋና ነገም መልካም እንደሚሆን እንቁጣጣሽ (የአዲስ ዘመን መለወጫ) በዓል አለፍን። እንቁጣጣሽም በተራዋ ሌሎች በዓላት ተራዋን አስረክባ ከደስታ ማግስት ሌላ የደስታ መንገድ ተረክበናል።

**እንቁጣጣሽ**
**እንኳን መጣሽ፤**
**በአበቦች መሃል**
**እንምነሽነሽ።**

እያልን የአበባዮሽ ሆይ! ዜማ እና ቅላፄ ከጆሯችን ሳይጠፋ፣ የቡና ጠጡ ስሜት ሳይርቀን፣ የአበባ ድምቀትና ውበት ሳይጠወልግ፣ የዕጣኑ መዓዛ እንዳወደን፣ የቄጠማው ውበት ሳይነጥፍ፣ የበዓሉም ድባብ ከቤታችን ሳይርቅ ደግሞ ይኸው የሙስሊም ወንድሞቻችን የመውሊድ በዓልን እና ከተራ በአንድ ላይ ከትመው መስከረም 16 አብረን ልንደምቅ ነው።

የመውሊድ በዓል የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ወ) የልደት በዓል ሲሆን፤ ይህም በዓል የሚከበረው ፍቅር ለማስረፅ፣ ክብራቸውን ከፍ ለማድረግ፣ ማኀበራዊ ትስስርን ለማጠናከር፣ ለዳዕዋና ለታሊም ጭምር በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ይከበራል። በዚህ በዓሉም በርካታ ወገኖች የሚዘያየሩበት፣ የተቸገረ የሚታገዝበት፣ ዕዝነት የበዛበትና የፍቅርና አንድነት ተምሳሌት በዓል ነው። መውሊድ ሙሃባ ነው፤ መውሊድ ፍቅር ነው፤ መውሊድ አንድነት ነው፣ መውሊድ ከዱኒያ ፍቅር የበለጠ ወደ ፈጣሪ የበለጠ የምንቀርብበት ቀንም ነው።

ከመውሊድ ማግስት ደግሞ መስከረም 17 ደግሞ የመስቀል በዓል ልናከብር ሽር! ጉድ! ላይ ነን። የበዓሉን ብዛትና በረከት የበለጠ ሊያንረው አንድነትና መተሳሰብን የበለጠ ሊያሳምረው በዚህ ወር በዓላት ከበራፋችን ላይ ቆመዋል። እነሆ! መስቀል ደረሰ።መንፈሳዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ጠፍቶ የነበረውን ቅዱስ መስቀል በንግሥት ዕሌኒ አማካኝነት መገኘቱን የሚዘክርበት በዚህም ሃይማኖቱ ተከታዮች ደስ የምንሰኝበት ዕለት ነው። ይህን መነሻ በማድረግ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ደመራ በመደመር የመስቀል በዓል በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ይከበራል።

የመስቀል በዓልን አክብረን ስናበቃ ደግሞ፤ ከሳምንት በኋላ ደግሞ ኦ! ያ ማሬ ሆ! ብለን እርጥብ ሣር ይዘን ፈጣሪን ልናመስግን ኢሬቻ በዓልን በጉጉት እየጠበቅን ነው። ኢሬቻ በዓል የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ‹‹ዋቃ›› ምስጋናውን ለማድረስ የኢሬቻ በዓልን ያከብራል ይላሉ ጥናታዊ ጽሑፎችና የገዳ ሥርዓት መረጃዎች ሲተነትኑት።

የኦሮሞ ሕዝብ ክረምቱ በማለፉ እና ወደ ብርሃን በመውጣቱና ለምለም ምድር በመመልከቱ በኢሬቻ ቀን ምስጋናውን ለፈጣሪ ያቀርባል። በክረምት ወራት ተራርቆ ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ በወርሃ መስከረም በደስታ እና ፈንጠዚያ ይገናኛል። ሕዝቡም ክረምቱን በፈጣሪ ፍቃድ የሞላው ውሃ ጎድሎ ከዘመድ አዝማድ አገናኘን ብሎ ለፈጣሪው ኦ! ያ! ማሬ ሆ! እያለ በአባ ገዳዎች እና ሃዳ ስንቄዎች ዝማሬ ታጅቦ ምስጋና ያቀርባል።

> **በዓሉቻችን የሁላችንም በዓል፤ የሁላችንም ድምቀት፤ የሁላችን ፍካት ስለመሆናቸው አስረግጠን መናገር፤ ከመናገርም ባለፈ በተግባር የምናሳይ መሆን አለበት፡፡ በአበቦች ሕብረ ቀለም አምረን ከአዲስ ዓመት ተሻግረን፤ በነብያችን መውሊድ ተደስተን፣ ከመስቀሉ በዓል አሸብርቀን፣ በእሬቻ ምስጋና በእርጥብ ሣር ተከበን ልንደምቅ እነሆ ይህን ወር ጀምረናል**

ይህ በዓል የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት በዓል ነው። ኢሬቻ የሰላም የአንድነትና የፍቅር በዓል ነው። በቀጣይ ሳምንት የምናከብረው የኢሬቻ በዓለም የእኛው ባህል መገለጫ ነው። ይህ በዓል በጋራ ምሥጋና የሚቀርብበት ሲሆን፤ በእሬቻ ውስጥ ያለውን እሴት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ እሴት እንዲሆንም መረባረብና ለኢትዮጵያ በሚጠቅም መንገድ ማስኬድ ተገቢ የሁላችንም ኃላፊነት ይሆናል።

እንግዲህ ወርሃ መስከረም በበዓል ድባብ የሁሉም እምነት ተቋማትና ሃይማኖቶች በሚባል ደረጃ ግጥምጥሞሽ የተፈጠረበት ወር ሆኗል፤ ደስም ይላል። ታዲያ እነዚህ በዓላት የጋራችን፣ የሁላችንም መድመቂያችን መሆናቸው ማሳየት ይጠበቅብናል። አንዱ ለሌላው ክብር ሊኖረው፤ ፍላጎቱንና እምነቱን ሊጠብቅበት የውዴታ ግዴታ መሆኑን ማሳየትም ማወቅም ይጠበቅበታል።

የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና የሀገሪቷ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ወዳጆች እና ተሰሚነት ያላቸው ግለሰቦች ለዚህ አንድነትና ፍቅርም የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል። የሁላችንም በዓል፤ የሁላችንም ድምቀት መሆኑን ለዓለም ሕዝብም ማሳየት የመላው ኢትዮጵያውያን ድርሻ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት ሀገሪቱን እየገጠማት ካለው ቀውስ ለማላቀቅ ሁነኛ መፍትሔ የመጠቆም ሀገራዊ፣ መንፈሳዊ ሙያዊ እና ሞራላዊ ግዴታም የምናሳይበት ወቅት ሊሆን ይገባል። ዛሬም፣ ነገም ከነገ ወዲያም የጋራ ሃብታችን የሆነችውን ኢትዮጵያን ማዕከል አድርገን አንድነታችን የምናሳይበት ጊዜም መሆን አለበት።

በዓሎቻችን የሁላችንም በዓል፤ የሁላችንም ድምቀት፤ የሁላችን ፍካት ስለመሆናቸው አስረግጠን መናገር፤ ከመናገርም ባለፈ በተግባር የምናሳይ መሆን አለበት። በአበቦች ሕብረ ቀለም አምረን ከአዲስ ዓመት ተሻግረን፤ በነብያችን መውሊድ ተደስተን፣ ከመስቀሉ በዓል አሸብርቀን፣ በእሬቻ ምስጋና በእርጥብ ሣር ተከበን ልንደምቅ እነሆ ይህን ወር ጀምረናል። 2016 የድምቀታችን፣ የአንድነታችን አንዱ በዓል የሌላችን መሆኑን የምናሳይት፤ የአንዳችን ደስታ የሌላችን እንዲሆንም በብርቱ የምንተጋበት አለፍ ሲልም ህመሞቻችን የምናጋራት ሊሆን ይገባል።

# ፍትሕ የናፈቁት - የሀገር ባለውለታ

ሙሉቀን ታደገ እና ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የዛሬው የፍረዱኝ ዓምድ ዝግጅታችን፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 በተለምዶ ልደታ ኮንዶሚኒየም ተብሎ ወደሚጠራው ሰፈር ይወስደናል፡፡ በጉዳይነትም ለልማት ከተነሱ ቤቶች የካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ውዝግብን ይዳስሳል፡፡

የነገሩ መነሻ፣ «በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 177 የተመዘገበ ቤቴ በ2002 ዓ.ም ለልማት የፈረሰ ቢሆንም፤ መንግሥት ለልማት ተነሺዎች መከፈል የሚገባውን የካሳ ክፍያ ሊከፍለኝ አልቻለም፡፡ በተፈጠረብኝ በመልካም አስተዳደር ችግር በጡረታ ዘመኔ ለከፋ ችግር ተዳርጌያለሁ፡፡ እየደረሰብኝ ያለውን በደል መንግሥትም፣ ሕዝብም ይወቅልኝ፤" ሲሉ ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ዝግጅት ክፍል አባሪ መረጃዎችን ጭምር በመያዝ በደል የፈጠረባቸውን ምሬት መግለጻቸው ነው፡፡

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ዝግጅት ክፍልም ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛን አቤቱታ መነሻ በማድረግ፣ እንዲሁም ከሰዎች እና ከሰነድ ያገኛቸውን ማስረጃዎች በመመርምር በማደራጀት የሚከተለውን ዘገባ አዘጋጅቷል፡፡

### ከአቤቱታ አቅራቢው አንደበት


የዛሬው ጡረተኛ ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ፣ ከውስጥ እና ከውጭ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ከተነሱ እና ከሚነሱ ጠላቶች ለመከላከል ከሀገሬ በፊት እኔ ብለው በ1951 ዓ.ም የውትድርና ሙያን ተቀላቀሉ፡፡ ሀገራቸውን በወታደርነት እያገለገሉ እያለም፣ በኮንጎ (ዛየር ግጭት ተቀሰቀሰ)፡፡ የተቀሰቀሰውን ግጭት ለማስቆም የተባበሩት መንግሥታት ለኢትዮጵያ ጥሪ አደረጉ፡፡ በጥሪው መሠረት ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ የሰላም አስከባሪ አባል ሆነው በ1954 ዓ.ም ወደ ሀገረ ኮንጎ አመሩ፡፡ በ1955 ዓ.ም በኮንጎ የነበረውን ግዳጃቸውን አጠናቀው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ፡፡

ከተመለሱ በኋላ ከደመወዛቸው ቆጥበው በቀድሞ አጠራር «ተክለሃይማኖት አውራጃ ከፍተኛ አራት ቀበሌ 49»፤ በአሁኑ አጠራር ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ወይም በተለምዶ ልደታ ኮንዶሚኒየም አካባቢ ለመኖሪያ ቤት የሚሆን ቦታ ገዝተው ቤትም ሰሩ፡፡ በቤቱም ለስምንት ዓመታት ተቀመጡ፡፡ እየኖሩ እያለ በኤርትራ የተደራጁ ቡድኖች በፈጠሩት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ምክንያት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛት ለግዳጅ ወደ ኤርትራ አቀኑ፡፡

ኢትዮጵያ በኤርትራ የተነሳውን ግጭት ሳትቋጭ በምስራቅ በኩል በሶማሊያ ተወረረች፡፡ ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛም ከኤርትራ ተነስተው ሶማሊያ ጥቃት ወደ ከፈተችበት ምስራቅ ኢትዮጵያ አመሩ፡፡ ኢትዮጵያም ከሶማሊያ የተቃጣውን ወረራን መክታ መለሰች፡፡

ከድል መልስ የ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ በደብረ ብርሃን ከተማ አካባቢ በሚገኝ የወታደር ማሰልጠኛ ወታደር የማሰልጠን ግዳጅ ተሰጣቸው፡፡ ወታደር እያሰለጠኑ ባሉበት ወቅት ሻቢያ የከፈተው ውጊያ አድማሱን እያሰፋ መጣ፡፡ በዚህም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኤርትራ ለግዳጅ ተላኩ፡፡ በኤርትራም ለስምንት ዓመታት ከስምንት ወር ቆዩ፡፡

ከስምንት ዓመታት በኋላ ወደ አዲስ አበባ በተመለሱ ጊዜ ግን ከደመዛቸው ቆጥበው የገዙትን ቤት የቀበሌ 49 ጽሕፈት ቤት ለግለሰቦች አከራይቶት አገኙት፡፡ ይህን ተከትሎ ጉዳዩን ለመንግሥት አቤት አሉ፡፡ መንግሥትም ቤቱ የራሳቸው ስለመሆኑ አምስት ምስክር እንዲያመጡ አዘዘ፡፡ አምስት ምስክር በማምጣት ቤቱ የእርሳቸው ስለመሆኑ በፍርድ ሸንጎ አስመሰከሩ፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ሸንጎ ታይቶ ቤቱ የእርሳቸው ስለመሆኑ ፍርድ ሸንጎ ሕጋዊ ማህተም እና ፊርማ እንዲሁም ቁጥር ያለበትን ሰነድ ለከፍተኛ አራት በማቅረብ ቤታቸው እንዲመለስላቸው ጠየቁ። ይሁን እንጂ የከፍተኛ አራት አስተዳደር ከከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ደብዳቤ ካላመጣህ በፍርድ ሸንጎ ውሳኔ ብቻ ቤቱን መመለስ አንችልም ሲሉ ይነግሯቸዋል፡፡



የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር
PROVISIONAL MILITARY GOVERNMENT
OF SOCIALIST ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT
AND HOUSING

የከተማ ቤት ባለቤትነት

ማረጋገጫ ደብተር

ቁጥር 4/23240

የተመዘገበበት ከተማ አ.አበባ

የባለቤትነት ደብተር አጠቃቀምና ግዴታ

1. ይህ ደብተር የሚሰጠው ንብረትነቱ ለተረጋገጠለት ግለሰብ ቤተሰብ ወይም ድርጅት ነው ።
2. ይህ ደብተር የሚሰጠው የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ባደረገው አዋጅ መሠረት የቤቱ ባለቤት ማን ስለመሆኑ ለመወሰን እንጂ የማዘጋጃ ቤቶች ሕግና ደንብ ከሚፈቀደው ውጭ የተሠሩ ቤቶችን ሕጉና ደንቡ እንዳይጸናባቸው ሊያደርግ አይቻልም ።
3. ይህ ደብተር ከጠፋ ፣ ከተቀደደ ፣ ከተበላሸ ወይም የማይነበብ ከሆነ ደብተሩ በእጁ ያለው ግለሰብ ቤተሰብ ወይም ድርጅት ወዲያውኑ ምትክ ደብተር እንዲሰጠው ለሰጭው መ/ቤት ማመልከት አለበት ።
4. የተፈቀደለት ቤት በተፈጥሮ አደጋም ሆነ ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ከጥቅም ውጭ ከሆነ ባለቤቱ ይህንኑ ለሰጭው መ/ቤት ማመልከት ወይም ደብተሩን መመለስ አለበት ።
5. ይህ ደብተር ቤቱ በሽያጭ ፣ በስጦታ ፣ በውርስ ወይም በሌላ ሕጋዊ መንገድ ለውል ተቀባዩ በስሙ ካልተዛወረ ለሌላ ግለሰብ ፣ ቤተሰብ ወይም ድርጅት አያገለግልም !

1


ማስጠንቀቂያ ፦
ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ያልጠበቀ ፣ በደብተሩ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ ማስረጃ ሰጥቶ የተገኘ ወይም የተመዘገበውን በሙሉ ወይም በከፊል የለወጠ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

ሰኔ 1972 ዓ.ም.

1 የቤቱ ባለቤት

1. ስም ፣ የአባትና የወንድ አያት ጭምር ፣
አሰፋ፡ አዱኛ፡ ታጋለው
2. ጾታ ወንድ ዕድሜ 50
ዜግነት ኢትዮጵያዊ
3. መሥሪያ ቤት — ሥራ ወይም
ማዕርግ ፶ አለቃ
4. የመኖሪያ አድራሻ ፣ ከተማ አ.አ
ከፍተኛ 13 ቀበሌ 05

2



በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 8 ዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ጽ/ቤት

LIDETA SUB CITY WEREDA 8 DESIGN & CONSTARUCTION
ADMINISTRATION DEVELOPMENT OFFICE

ል/ክ/ከ/ወ/8/ዲ/ግ/ል/ጽ/ /04

ቀን 06/06/2004 ዓ.ም

በየካ ክፍለ ከተማ
ለወረዳ 4 ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- መረጃ ስለመጠየቅ

በደብዳቤ ቁጥር የካ/ወ4/2279/04 በቀን 02/06/2004 ዓ.ም በተፃፈልን ደብዳቤ የቀድሞ ቀበሌ 49 ውስጥ የቤት ቁጥር 177 የሆነውን ቤት መረጃ እንድንሰጥ ተጠይቀናል፡፡ በመሆኑም ቀበሌው በልማት እንደፈረሰ ይታወቃል እንዲሁም ይህ ቤት በወቅቱ መንግስት የማያስተዳድረው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር
አብርሃ ተ/ሃይማኖት
የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ

ይህን ተከትሎ ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ስለጉዳዩ በማመልከቻ አሳወቁ፡፡ ሚኒስቴሩም ጉዳዩን ሲመረምር ቆይቶ ቤቱ የ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ መሆኑን አረጋግጦ የባለቤትነት ደብተር ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህ ደብተር በተጨማሪ ቤቱን በአስቸኳይ እንድታስረክቡት የሚል ደብዳቤ ለከፍተኛ አራት ከነማ ነዋሪዎች ማህበር ጽሕፈት ቤት መጻፉን ይናገራሉ፡፡

በመቀጠል «ቤቴን አስረክቡኝ» ሲሉ በከፍተኛ አራት የቀበሌ 49 ክልል አስተዳደሩን ጠየቁ። የቀበሌውም ምላሽ ግን «በቤቱ ሰዎች አሉ፤ ሰዎቹ ቤት ሰርተው ሲወጡ በዚያ ጊዜ ጠይቀን» የሚል ሆነ፡፡ «እኔ በኪራይ ቤት ተቀምጬ እንዴት እንዲህ ይደረጋል?" ሲሉ ቀበሌውን መጠየቃቸውን ያስረዳሉ፡፡

የቀበሌ 49 አስተዳደር የወሰነውን ውሳኔ ተከትሎ ጉዳዩን ለከፍተኛ አራት አሳወቁ፡፡ ከፍተኛ አራት ለመሸንገል በሚመስል መልኩ በአካባቢው የሚገኝ የቀበሌ ቤት አፈላልግና ስታገኝ ቤቱን እንሰጥሃለን ሲል አዘዘ፡፡ በዚህም የ፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ እኔ የምኖረው እንጦጦ አውራጃ ከፍተኛ 13፤ እንዴት ተክለሃይማኖት አውራጃ የሚገኝን ባዶ ቤት ላውቅ እችላለሁ? ከፍተኛ አራት ይህን ማለቱ ትክክል አይደለም! ሲሉ የከፍተኛ አራትን የውሳኔ ሃሳብ መቃወማቸውን ይናገራሉ፡፡ ይህን ተከትሎ ከፍተኛ አራት ጉዳዩን በመመልከት ቀጠሮ ሰጥቶ አሰናበታቸው፡፡ በተቀጠሩበት ቀን ቢመለሱም ጉዳያቸው ሊፈታ አለመቻሉን ይገልጻሉ፡፡

በዚህም ጉዳያቸውን ወደ አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ወሰዱት፡፡ ማዘጋጃም ውዝግብ የተነሳበት ቤት የአንተ ስለመሆኑ ምን ማስረጃ አለህ? የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡ ፶ አለቃ አሰፋም የቤት ባለቤትነት ደብተር አለኝ በማለት የቤት ባለቤትነት ማረጋጋጫ ደብተራቸውን አሳዩ፡፡ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ሕጋዊ መሆኑን ያረጋገጠው የማዘጋጃ ቤትም 10 ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቤቱን አስረከባችሁ ምላሻችሁን እንድታሳውቁኝ የሚል ደብዳቤ ለከፍተኛ አራት ፃፈ፡፡

ይህን ተከትሎ ከፍተኛ አራትም ቤቱን የያዙትን ሰዎች አስለቅቀን እስከምናስረክብ የ፶ አለቃ አሰፋ ባለበት ቤት ኪራይ እንዳይከፍሉ የሚል ደብዳቤ ጃንሜዳ አካባቢ ለሚገኝ እንጦጦ አውራጃ ከፍተኛ 13 ጻፈ፡፡ በዚህም ጃንሜዳ አካባቢ በሚኖሩበት የቀበሌ ቤት በነፃ ተቀመጡ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለሚኖሩበት ቤት ኪራይ ባይከፍሉም ልደታ ለሚገኘው እና ለሰሩት ቤት ግን ግብር የሚገብሩት እርሳቸው ነበሩ፡፡

ልደታ ለሚገኘው ቤት ግብር ከመክፈል ጎን ለጎን፣ ቤታቸው እንዲመለስላቸው ለበርካታ ጊዜያት እየተመላለሱ ከፍተኛ አራትን ቢጠይቁም መልስ የሰጣቸው አካል አልተገኘም፡፡ በዚህ ሂደት ላይ እያለ በ2002 ዓ.ም ሳይኖሩበት ግብር ሲከፍሉበት የነበረው ቤት ለልማት በሚል ፈረሰ፡፡ ከፈረሳው በኋላ ለልማት በሚል ከቦታቸው ለሚነሱ ሰዎች የሚደረግላቸው የመብት ማስከበር ሥራ ለእርሳቸውም እንዲሰጣቸው የልደታ ክፍለ ከተማን ጠየቁ፡፡ ክፍለ ከተማውም የእናንተ ቤት የተካካሰ ነው፡፡ ትንሽ ጊዜ ቆዩ እና ካሳ ይከፈላችኋል ተብለው የካሳ ክፍያቸውን እየተጠባበቁ እያለ በ2010 ዓ.ም ሀገራዊ ለውጥ መጣ፡፡

በለውጡም ችግራቸው እንዲፈታላቸው በማሰብ ያልደረስኩበት ቦታ የለም የሚሉት ፶ አለቃ አሰፋ፤ ጉዳዩ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ ከንቲባ ቢሮ ሄደው እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ከንቲባ ቢሮ ደግሞ ጉዳዩን የአዲስ አበባ መሬት ልማትና አስተዳደር ይፈታዋል ብሎ እንደጠቆማቸው፤ መሬት አስተዳደር ደግሞ ተግባረ ዕድ አካባቢ ለሚገኝ የካሳ ጉዳዮች ሰሚ ጉባዔ እንደላካቸው፤ የካሳ ጉዳዮች ሰሚ ጉባዔ ደግሞ የልደታ ክፍለ ከተማ ስለጉዳዩ ካልመራልህ አልቀበልህም ማለቱን ይገልጻሉ፡፡

፶ አለቃ አሰፋ አዱኛ፣ የተቋማቱን የፋይል አያያዝ ችግርን አስመልክቶ ግርምት በተላበሰ ስሜት ስለ ጉዳዩ ሲያስረዱ፤ «የሚገርመው ነገር፣ ክፍለ ከተማ በሄድኩ ወቅት በደርግ ዘመነ መንግሥት ከከተማ ልማት ያመጣኋትና ቤቱን አስረክቡት የምትለው ደብዳቤ ብቻ በእኔ ማህደር ተገኘች፤" በማለት ነበር። ይህን ተከትሎ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ማህደራቸው እንደሚገኝ ከክፍለ ከተማ ተጠቁመው ወረዳ 09 መላካቸውን ይናገራሉ፡፡ ወረዳ 09 ሲሄዱ ፋይላቸውን ለማየት የአንድ ወር ቀጠሮ እንደሰጣቸው እና ከወር በኋላም ወደ ወረዳው ሲመለሱ "በእኛ የሚፈፀም ነገር የለም፡፡ ብትፈልግ ክሰስ" የሚል መልስ እንደሰጣቸው ያስረዳሉ፡፡

ይህን ተከትሎ ጉዳዩን ፍርድ ቤት ወስደውት እንደነበርም ያስታውሳሉ፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከማሳረፍ ይልቅ፣ "ይህ ጉዳይ የሚመለከተው የልደታ መሬት ልማትና አስተዳደር እንጂ እኛን አይደለም" የሚል ምላሽ እንደሰጣቸው የሚናገሩት ፶ አለቃ አሰፋ፤ በዚህም እስከ ዛሬ ድረስ ጥያቄያቸው ምላሽ አለማግኘቱን ይናገራሉ፡፡

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

# ፍትሕ የናፈቁት -...

ከገጽ 6 የዞረ

በዚህ መልኩ ፍትሕ አጥተው ከፍተኛ ችግር ውስጥ መሆናቸውን የሚናገሩት ፱ አለቃ አሰፋ፣ "አሁን ላይ አቅም አጣሁ፣ ፍትህም አጣሁ፣ በሰው ሀገር ደምቼ እና ቆስዬ ባገኘሁት ገንዘብ የሰራሁትን ቤት ተነጠቅሁ፡፡ ሲሆን ለሀገሬ የደከምኩኝ ለሀገሬ የለፋሁ ሰው ልደገፍ ይገባኝ ነበር፡፡ ካልሆነ ደግሞ በደሜ እና በላቤ የሰራሁትን ቤት መቀማት አልነበረብኝም፡፡ እውነት ኢትዮጵያ ለእኔ ውለታዬን እንዲህ ነበር መክፈል የሚገባት?" ሲሉ ሃሳባቸውን በጥያቄ አቅርበዋል፡፡

ምንም እንኳን በማካካሻነት በወሰዱት ቤት ዛሬም ኪራይ የማይከፍሉ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት የሚገኙበት ቤት ለልማት ከፈረሰው ቤት በጥራትም ሆነ በስፋት ሊወዳደር እንደማይችል የሚገልጹ ፱ አለቃ አሰፋ፣ እርሳቸው የሰሩት ቤት 150 ካሬ ላይ ያረፈ ሁለት መኝታ ቤት፣ መጸዳጃ እና ማብሰያ ቤት ያለው እንደነበር ነበር ይገልጻሉ፡፡ «በማካካሻነት የተሰጣቸው ግን ለመኖር አስቸጋሪ የሆነ እና ለአዛውንት ምቹ ባለመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ለፈረሰው ቤት ተገቢውን ካሳ ማግኘት እችል ዘንድ በመተባበር የበኩላችሁን ተወጡ» ሲሉ አዛውንቱ ፱ አለቃ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

### ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎች

**ሰነድ አንድ፡-** ሰኔ 19 ቀን 1972 ዓ.ም የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ለ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ በቁጥር 4/23240 በተመዘገበ ሰነድ ላይ የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መስጠታቸውን ያትታል፡፡

**ሰነድ ሁለት፡-** አዲስ አበባ አጠቃላይ ነዋሪዎች ማህበር ምክር ቤት በቀን 29/9/1977 ዓ.ም በቁጥር ከ4/ቀ49 /የፍመቀ /299/1 ለከፍተኛ አራት ከነማ ጽሕፈት ቤት የተጻፈ ደብዳቤ ነው፡፡ ደብዳቤውም፣ በከፍተኛ አራት ቀበሌ 49 የቤት ቁጥር 177 ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት የ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ ስለመሆኑ በፍርድ ሸንጎ አስመስክረዋል፡፡ ስለሆነም ከቤቱ ጋር ተያይዞ ለሚጠየቀው የመብት ጥያቄ አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው ሲል ይገልፃል፡፡

**ሰነድ ሦስት፡-** የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በቀን 07/10/1977 ዓ.ም፣ በቁጥር ከቤ/ከ4/ቀ49/2490/77 ለከፍተኛ አራት ከነማ ነዋሪዎች ማህበር ጽሕፈት ቤት በጻፈው ደብዳቤ እንደጠቀመው የ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ በከፍተኛ አራት ቀበሌ 49 የቤት ቁጥር 177 ተመዝግቦ በሚገኘው ቤት ላይ የባለቤትነት ማስረጃ ከፍርድ ሸንጎ ቢያስመሰክሩም የከፍተኛ አራት ከነማ ነዋሪዎች ማህበር ጽሕፈት ቤት ከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ደብዳቤ ካላመጣህ የባለቤትነት ጥያቄውን አንቀበልም ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከፍርድ ሸንጎ የተመሰከረበት ማስረጃ በከፍተኛ አራት ከነማ ነዋሪዎች ማህበር ጽሕፈት ቤት እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በጉዳዩ ላይ ውሳኔ በመስጠት ለከፍተኛ አራት ከነማ ነዋሪዎች ማህበር ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ ይችል ዘንድ የከፍተኛ አራት ከነማ ነዋሪዎች ማህበር ጽሕፈት ቤት ማስረጃውን እንዲልክልን እናሳስባለን የሚል ነበር፡፡

ይህን ተከትሎ ከፍተኛ አራትም በአዲስ አበባ አጠቃላይ ከተማ ነዋሪዎች ማህበር ምክር ቤት ሥም በቁጥር ከ4/16852/77 በቀን 25/10/1977 ዓ.ም ለከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በላከው ሰነድ እንዳረጋገጠው ውዝግብ የተነሳበት ቤት የ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ ስለመሆኑን አረጋግጧል፡፡

**ሰነድ አራት፡-** በቀን 27/5/1981 ዓ.ም የከፍተኛ አራት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ላይ የተገኘ ማስረጃ እንደሚመለከተው፡- አንደኛ ቤቱ በቅጽ 004/014 ተሞልቶ በማህደራቸው ውስጥ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም በቤቱ አበል አልበሉበትም፡፡ ሁለተኛ ቤቱን ከአዋጅ በፊትም ሆነ በኋላ በመኖሪያ ቤት እንጂ በድርጅትነት አልተያዘም በተጨማሪም ከአዋጁ በኋላ ሌላ ቤት አልሸጡም፡፡ ሦስተኛ ቤቱ የግላቸው ስለመሆኑ በ15/9/1977 ዓ.ም በቀበሌው ፍርድ ሸንጎ በሶስት የሕግ ምስክሮች የተረጋጋጠ ሰነድ በፋይላቸው ውስጥ ይገኛል፡፡ አራተኛ በቤቱ አበል አያገኙም፣ ቤቶችንም አላስረከቡም የሚል ነው፡፡ ይህ ቃለ ጉባዔ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የተላከ ነው፡፡



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

መ/ፂ1/3/7 ሴሪ/አአከአ/4/ሰ

የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

የገቢ ደረሰኝ

ቀበሌ 07 ቀን 22/1/2001 № 366502


ስም አሰፋ አዱኛ መለያ 17662 የማህደር ቁ 8/07/14/4267

| የክፍያ ምክንያት | ዘመን | የክፍያ መጠን | መቀጫ | የገንዘብ ልክ |
|---|---|---|---|---|
| የከተማ ቤት ኪራይ ፡ የቤት ቁ 177 | 2001 | 3.12 | 0.00 | 3.12 |
| የከተማ ቤት ግብር ፡ የቤት ቁ 177 | 2001 | 0.96 | 0.00 | 0.96 |
| | | | ድምር | 4.08 |

የገንዘብ ልክ በፊደል አራት ብር ከ ስምንት ሳንቲም

ፈራሚ ስም

የገንዘብ ተቀባይ ስምና ፊርማ



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

የግብርና ታክስ መሰብሰቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

የገቢ ደረሰኝ

ቀበሌ 07 ቀን 9/7/2001 № 055287

ስም ካሳ ሹሜ ገመዳ መለያ 3498

| የክፍያ ምክንያት | ዘመን | የክፍያ መጠን | መቀጫ | የገንዘብ ልክ |
|---|---|---|---|---|
| ኪራይ ከ የካቲት እስከ መጋቢት 2001 - የቤት ቁ | 2001 | 15.00 | 0.00 | 15.00 |
| | | | ድምር | 15.00 |

አስራ አምስት ብር

ኦሪጂናል

የገንዘብ ተቀባይ ስምና ፊርማ

በአንድ ቤት የሁለት ግብር ከፋዮች ደረሰኝ፣

**ሰነድ አምስት፡-** የአዲስ አበባ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ምክር ቤት በቀን 2/8/1981 በቁጥር ከ4/985/81 ለከፍተኛ አራት ለቀበሌ 49 ከነማ ጽሕፈት ቤት በጻፈው ደብዳቤ እንዳመለከተው በቀበሌ 49 በቤት ቁጥር 177 ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት የ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ ስለሆነ ቤቱ ለ፱ አለቃ አሰፋ እንዲለቀቅላቸው እናስታውቃለን የሚል ነው፡፡

**ሰነድ ስድስት፡-** የተክለሃይማኖት አውራጃ አስተዳደር በቁጥር ከ/269/49/82 በቀን 25/1/1982 ዓ.ም ለቀበሌ 49 ከነማ ጽሕፈት ቤት በፃፈው ደብዳቤ እንዳመለከተው በቀበሌ የሚገኘው የቤት ቁጥር 177 የሆነ ቤት ባለንብረት የሆኑት ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ ቤታቸው በተከራይ የተያዘ በመሆኑ እንዲለቀቅላቸው በከፍተኛ አራት ከነማና ከአዲስ አበባ አስተዳደር አካባቢ ጽሕፈት ቤት ትዕዛዝ የተላለፈላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡

የአመልካቹን ቤት መለቀቅ አስመልክቶ የአዲስ አበባ አስተዳደር አካባቢ ጽሕፈት ቤት ግንቦት 24 ቀን 1981 በቁጥር አም12/4/27 በተጻፈ ደብዳቤ፣ አመልካች በከፍተኛ 13 ቀበሌ 05 ውስጥ ተከራይተው የሚኖሩበት የቤት ቁጥር 907 የሆነ ቤትና ሊለቀቅላቸው የሚገባው በከፍተኛ አራት ቀበሌ 49 የሚገኘው ቤት ኪራይ እኩል ስለሆነ በአመልካች ቤት ያሉ ተከራዮች ወደ ከፍተኛ 13 ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር ተዛውረው የ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ ቤት እንዲለቀቅ መመሪያ የተሰጠ ከመሆኑም በላይ በመመሪያው መሠረት፣ እንዲፈፀም የከፍተኛ አራት ከነማ ጽሕፈት ቤት ግንቦት 28 ቀን 1981 ዓ.ም በቁጥር ከ4/1259/81 በተጻፈ ደብዳቤ ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡

ሆኖም የቀበሌው ጽሕፈት ቤት እንደ ትዕዛዙ መፈጸም ሲገባው ትዕዛዙን ካለመፈጸሙም በላይ የገጠመውን ችግር እንኳን አልገለፀም፡፡ በዚህ ምክንያት አመልካቹ ከፍተኛ መጉላላት እየደረሰባቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ አስተዳደር አካባቢ ጽሕፈት ቤት በቁጥር አም 1214/27 እና ከከፍተኛ አራት ከነማ በቁጥር ከ4/1259/81 በተጻፉ ደብዳቤዎች መሠረት ተፈጻሚ ውጤቱ ከጥቅምት 10 ቀን 1982 በፊት እንዲገለጽልን በጥብቅ እናሳስባለን የሚል ነው፡፡ በዚህ ሰነድ የተመለከተው ቤቱ ለ፱ አለቃ አሰፋ እንዲመለስ ነበር፡፡

**ሰነድ ሰባት፡-** የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ዲዛይን እና ግንባታ አስተዳደር ልማት ጽሕፈት ቤት በቀን 06/06/2004 ዓ.ም በቁጥር ል/ክ/ክ/ወ/8/ ዲ/ግ/ል/ጽ0567/04 ለየካ ክፍለ ከተማ ለወረዳ 04 ሥራ አስኪያጅ ጽሕፈት ቤት በተፃፈ ደብዳቤ እንደተጠቀሰው፣ ውዝግብ የተነሳበት ቤት በቀበሌው በልማት እንደፈረሰ እና ይህ ቤት በወቅቱ መንግሥት የማያስተዳድረው መሆኑን የገለጸበት ደብዳቤ ነው፡፡

### የልደታ ክፍለ ከተማ ምላሽ

በጉዳዩ ላይ ምላሽ የሰጡን የልደታ ክፍለ ከተማ የመሬት ዝግጅትና ማስተላለፍ ሥራዎች ዘርፍ አቶ ቴዎድሮስ ፀጋዬ ሲሆኑ፣ ጉዳዩን በዝርዝር ለማየትም ሆነ ለመወሰን ሕጎች፣ አዋጆችና፣ መመሪያዎች ምን እንደሚሉ መገንዘብ ተገቢ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ እኔ የምሠራበት ዘርፍ መብት ከተፈጠረ በኋላ የሚያስተናግድ እንጂ መብት ያልተፈጠረለት አካል ለሚያቀርበው ቅሬታ ምላሽ የምንሰጥበት አግባብ የለም ብለዋል፡፡

ይሁንና ግን እንደ ዜጋ አንድ ግለሰብ ሲበደል ወይንም ፍትህ ሲዛባ እንመለከትም ማለት አይደለም የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ፣ ፱ አለቃ አሰፋ አዱኛ ሕጋዊ አካሄድን ጠብቀው የሚመጡበት አግባብ ከተፈጠረ በአስተዳደራዊም ሆነ በሌላ ሕጋዊ አካሄድ እልባት ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ጉዳዩን በተመለከተ የልደታ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ነጂባ አብደላ፣ የዝግጅት ክፍላችን በምርመራ ባገኛቸው ሰነዶች ላይ ባለሙያዎች ማብራሪያ ይሰጣሉ ቢሉም፣ ከተቋማቸው ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ዝርዝር መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ባለሙያዎችን ማግኘት አልተቻለም፡፡ ለዚህ ደግሞ ባለሙያዎቹ እንደ ምክንያት የሚያነሱት፣ ጉዳዩ ባለሙያዎቹ ተመልክተው የሚፈቱት ወይንም ማብራሪያ የሚሰጡበት ሳይሆን፣ ከጉዳዩ ውስብስብነት አኳያ አስተዳደራዊ መልክ ያለው ነው፡፡

አያይዘውም ጉዳዩ የባለሙያዎችን ሳይሆን የበላይ ኃላፊዎችን ማብራሪያ የሚጠይቅ እንደሆነም በመግለጽ፣ ጉዳዩ ሕጋዊ አግባብን ጠብቆ የሚመጣ ከሆነ፣ እንዲሁም የበላይ ኃላፊዎች ይሁንታ እና ትዕዛዝ ከታከለበት ፱ አለቃ አሰፋን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆናቸውንም ባለሙያዎቹ አረጋግጠዋል፡፡

### የዝግጅት ክፍሉ ግኝት

**አንደኛ፣** በአሁኑ ወቅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ መልካም አስተዳደር እና ምርመራ ክፍል፣ ከልደታ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ያገኘው የሲአይ ኤስ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ቤቱ በቁጥር 177 የቀበሌ ቤት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህ የሲአይ ኤስ ሰነድም የ፱ አለቃ አሰፋ በግል ቤትነት ማረጋገጫ ይዘው ግብር ሲከፍሉበት ከቆዩባቸው ሰነዶች ጋር የሚጣረስ ብቻ ሳይሆን፣ በአንድ ቤት ላይ ሁለት ዓይነት አሰራር የተከተለ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይሄም የመረጃዎችን አሻሚነትና የአሰራር ችግር መኖሩን ለመገንዘብ አስችሏል፡፡

**ሁለተኛ፣** የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ለ፱ አለቃ አሰፋ ከሰጣቸው የከተማ ቤት ማረጋገጫ ሰነድ ጋር የተቃረነ ነው፡፡

**ሦስተኛ፣** የዝግጅት ክፍላችን በምርመራ ካገኛቸው ሰነዶች መካከል፣ በዚሁ ቤት ከ፱ አለቃ አሰፋ በተጨማሪ በ2001 ዓ.ም በአንድ ሌላ ግለሰብ ስም የቤት ግብር ሲከፈል እንደነበር፣ ግለሰቡም በቦታው ምትክ በቁርቆስ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሳይት ባለ ሁለት መኝታ ቤት መውሰዳቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ይገኝበታል፡፡

### የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት

ውድ አንባቢያን በጉዳዩ ዙሪያ ከተገኙ ሰነዶችና ማስረጃዎች፣ እንዲሁም ከመረጃ ሰጪ ተቋማት መረጃን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን አኳያ ጉዳዩ ሰፋ ያለ ምርመራ የሚጠይቅ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የምርመራውን ውጤት በሚቀጥሉት ዝግጅቶቻችን የምናሳውቅ ይሆናል፡፡

በተያያዘም፣ የዝግጅት ክፍላችን፣ መረጃ ለማግኘት ከተቸገረባቸው ተቋማትና ኃላፊዎች መካከል የልደታ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ነጂባ አብደላ ለሚነሳላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ የተሟሉ መረጃዎችን ይዘን እንደምንቀርብ ከወዲሁ እንገልጻለን፡፡

# ሰላም የምትጠይቀውን ዋጋ ሁሉ ከፍላችሁ ግዟት እንጂ በፍጹም አትሽጧት!

በጋዜጠኛና ሲኒየር የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ሳንዱዘር አሥራት

ሰላም ከበጎ ህሊና እና ንጹሕ ልብ የሚመነጭ ፣ ለራሳችንና ለሌሎች ሁለንተናዊ መረጋጋትና የሀሳብ መቃናት፤ የግል ጥቅሞቻችንን ተሻግረን የምንከፍለው በየደረጃው በተግባር የሚገለጽ ውድ ዋጋ ነው።

ሰላም በነፍስ ወከፍ ከእያንዳንዱ ሰው ለሌሎች፣ ከሌሎችም ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ መረጋጋት ፣ የሀሳብ መቃናት ፣ ማኅበራዊ እረፍት ማግኘት ፣ዘርቶ መቃም፣ ወልዶ መሳምና የህይወት መሻሻል ከግል ጥቅም መጠበቅ ባለፈ ለብዙኃን የሚከፈል በምንም አይነት መለኪያ ልተመን የማይችል ርካታና ውስጣዊ ደስታን ጭምር የሚፈጥርም ይሆናል።

በየደረጃው የሚገለጽ የሰላም ጥረት በተገኙበት ሁሉ እያደረጉ ያሉ ዜጎችን የሚገልጽ ባይሆንም ፤በተለምዶ የራሳችንን ፣የአካባቢያችንንና የሀገራችንን ሰላም ሕዝባዊ ተልዕኮና አደራ የተሰጣቸው ውስን አካላት ብቻ እንዲያስጠብቁልን አዘውትረን የምንፈልግ መሆኑ ዘላቂ የሰላም ግንባታ እንቅስቃሴያችን የሚፈለገውን ያህል ውጤት እንዳያመጣ አድርጎታል።"ጥንታዊ የባቢሎን ሰዎች የጋራ ከተማቸውን ለመገንባት እያንዳንዳቸው ጡብ እንዳቀበሉ ሁሉ "የየድርሻችንን የሰላም አስተዋጽኦ ከግል ጥቅም ስሌት በጸዳ መልኩ ስለሌሎችና ሀገር ዘላቂ ዕድገት ማበርከት ማኅበራዊ ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት መቻል ከመሆኑም ባለፈ የዜግነት ግዴታም ጭምር መሆኑ የሚዘነጋ አይሆንም።

"ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" እንደሚለው የታላቁ መጽሐፍ የሰላም መልዕክትና እንደ ሌሎችም ሃይማኖቶች የሰላም አስተምህሮ ሁሉ"ዘወትር ስለ-ሰላም ገደቦችን ሁሉ አልፈን በመሄድ በማኅበራዊ መስተጋብራችን ለሚገኙን ሰዎች ፣ ከፍ ሲልም ለዜጎችና እና ሀገር ሁለንተናዊ ሰላምና መረጋጋት የበኩልን የነብስ ወከፍ ማኅበራዊ ኃላፊነት ያለቀስቃሽ በሚገባና በሚመጥን መልኩ መወጣት መቻል የጋራ ሰላምን ለማረጋገጥና ለማጽናት አስተዋጽኦው የላቀ እንደመሆኑ ከአዳራሽ ግርግር ባለፈ የሁሉንም ተግባራዊ ተጨባጭ የሰላም ጥረት የሚጠይቅ ነው።

የሰላም ጥረትን ወደ ሌሎች የሚገፉና ከሌሎች የሚጠብቁ አካላት የሚፈጥሩትን ውስን ክፍተት በመጠቀም በተቃራኒው ኃላፊነት የጎደላቸው አንዳንድ ግለሰቦች በህቡዕ አደረጃጀት በመሰባሰብ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለግጭት መንስኤ የሚሆኑ አጀንዳዎችን በማዋለድ እንደተጠመዱ ይገኛሉ። ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ በመፈለግ በዜጎች ሕይወትና የትውልድ ዕጣ ፋንታ ላይ ቁማር እየተጫወቱ የሚገኙ መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ሰነባብቷል። በየደረጃው ግጭት የማዋለድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኃይሎች በሚያገኙት የሚዲያ አማራጭ ሁሉ እያስተላለፉ እንደሚገኙት ለአንድነት የማይበጅ አፍራሽ መልዕክት አማካኝነት ለሁላችንም ግልጽ አድርገው እያሳዩን እንደመሆናቸው በዚህ ረገድ የሀገር አንድነትን ለመከላከል መሰባሰብ ከሁሉም የሚጠብቅ ነው።

ውድ ሀገራችንን ጨምሮ፣ በተገኘንበት የዓለም ዳርቻ ሁሉ ስለ ሰው ልጆች ሁለንተናዊ እረፍትና መረጋጋት ምክንያት እንጂ፤የሰላም እጦት መንስኤ ሆነን ላለመገኘት ራሳችንን መግዛት፣ ማረቅና መግራት ፣ሰላምን ለሁሉም መተው ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ማኅበራዊ ኃላፊነት ከመሆኑም ባለፈ የዜግነት ግዴታም ጭምር እንደሚሆን ይታሰባል። ከዚህም በተጓዳኝ ለእያንዳንዱ የሰላም እጦት ክስተት ራስን የመፍትሔ አካል አድርጎ ማቅረብ ደግሞ በሁሉም ረገድ የሚገለጽ ዘላቂ ሰላምን በተገኘንበት የሀገራችን ክፍል ሁሉ ለማስፈን፤ የሚያስችለን እንደመሆኑ ዘወትር በነብስ ወከፍ ዕለት - እለት ስለ አካባቢያችን ሰላም የበኩላችንን ተደማሪ አስተዋጽኦ በሚፈለገው ልክና አግባብ ማዋጣት የተገባን መሆኑ ግልጽ እንጂ ሌሎች በቅስቀሳ መልክ ግንዛቤ የሚፈጥሩልንና የሚያስረዱን ሊሆን አይገባም።

ትናንት በታሪካችን ላጋጠመን ስብራት ሁሉ፤

> የሰላም ጥረትን ወደ ሌሎች የሚገፋና ከሌሎች የሚጠብቁ አካላት የሚፈጥሩትን ውስን ክፍተት በመጠቀም በተቃራኒው ኃላፊነት የጎደላቸው አንዳንድ ግለሰቦች በህቡዕ አደረጃጀት በመሰባሰብ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለግጭት መንስኤ የሚሆኑ አጀንዳዎችን በማዋለድ እንደተጠመዱ ይገኛሉ

የሀገርን ህልውናና ቀጣይነት ማዕከል ያደረጉ አካታችና እውነተኛ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ መቻል፤የነገ ዕጣ ፈንታችን ለመወሰን አስተዋጽኦው የላቀ መሆኑ አያጠያይቅም። ቀጣይ የሀገር ግንባታ ራዕያችንን ጨምሮ ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን በምንገኝበት የምስራቅ አፍሪካ ቀጠናና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስከበር እንዲያስችለን ፤እውነተኛ ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን መገንባትና ፍጹም በማይነጣጠል ወንድማማችነት በአንድነት መቆም የሚገባን መሆኑን በታሪካችን የተመለከትነው የጋራ ጥንካሬያችን ምሳሌያችን ነው። ዘመናትን የዘለቀውን በመከባበር ፣ በአብሮነትና በወንድማማችነት ጽኑ መሠረት ላይ የቆመውን በዓለም የተመሰከረለትን ኢትዮጵያዊ አንድነት ጠብቀን ከማስቀጠል ውጪ ለሁላችን የሚሆን ሁለተኛ ምርጫ ፈጽሞ ሊኖረን እንደማይችል ለሁላችንም ግልጽ በመሆኑ መሰባሰባችን ተጽዕኖችንን በይበልጥ ከፍ የሚያደርገው ይሆናል።

አሁን በምንገኝበት ወቅት እንደ ሀገር፣ ከውስጥና ከውጭ በርካታ ሕብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን ፣ ዘመናትን የተሻገረ ወንድማዊ አብሮነታችንን የሚገዳደር ፈተና ተጋርጦብናል። የእርስ በርስ ጦርነትን ጨምሮ በርካታ ማኅበራዊ ፖለቲካዊና የገበያ ውንብድና እንዲሁም አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪን ያካተተ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ለሰላም እጦት መንስኤ ከመሆኑም ባለፈ የዜጎችን ሕይወት እያከበደውም መሆኑም ይስተዋላል ።ሀገር ከውስጥም ከውጭም በሚሰነዘርባት ልዩ ልዩ ቀውስ የሚፈጥር ሁኔታ ውስጥ እያለፈች ባለችበት በዚህ ጊዜ፤ እያንዳንዱ ሀገሩን የሚወድ ዜጋ የእለት -ዕለት ተግባሮቹን በሚያከናውንበት ወቅት ሁሉ በተጓዳኝ ለሰላም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በሁሉም ዘንድ በፍጹም ቸል ልባል የሚገባው አይሆንም።

የሀገርን ሁለንተናዊ ሰላምና መረጋጋት የሚሻ የትኛውም የዲጂታልና የሳይበር ሚዲያ የመረጃ መለዋወጫ አማራጭ ተጠቃሚ ሁሉ፤በየደረጃው ያልተጣራና ሀሰተኛ ግጭት አባባሽ መልዕክት ከማጋራት በመቆጠብ የመፍትሔ አካል መሆን የሚጠበቅበት ይሆናል።

በኢትዮጵያ አሁናዊ ተጨባጭ ሁኔታ፣ መንግሥት ሰላምን ለማረጋገጥ በየደረጃው ከሚወስዳቸው እርምጃዎች በተጓዳኝ የሃይማኖት ተቋማት ፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች ፣ፖለቲከኞች ፣ሊህቃን፣በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ሰላም ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዜጎችና ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች የመፍትሔ አካል ሆነው የየድርሻቸውን ማኅበራዊ ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት የሰላም ሂደቱን ሊደግፉ እንደሚገባ በበርካቶች እየተጠየቀ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል።

ከሕዝብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሚኖራቸው ፖለቲከኞች፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ማኅበራዊ አንቂዎችና ሌሎችም አካላት ፤ በቀውስ ወቅት የሚደረጉ የተግባቦት ባህሪያትን ማዕከል ባደረገ መልኩ በመንቀሳቀስ ግጭት ከሚያባብሱ ድርጊቶች ተቆጥበው ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት መቻል ለሀገር ሁለንተናዊ መረጋጋት አስተዋጽኦ የጎላ ነው።

በበርካታ ሀገራትና በዓለም ላይ፤ ግጭቶች ተወግደው ሰላምና እርቅን ለማስፈን እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች በሙሉ የአሳታፊነት ውስንነት ስለሚገጥማቸውና እያንዳንዱ ግለሰብ ለአካባቢው፣ ለሀገሩና ለዓለም ሁለንተናዊ ሰላም በሚፈለገው ልክ የድርሻውን ማህበራዊ ኃላፊነት መወጣት ባለመቻሉ ሳቢያ አንጻራራዊ ሰላም እንጂ ፋይዳው የላቀ ዘላቂ ሰላም በዓለም ላይ ለማስፈን አልተቻለም ።

አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሰላም ድርድር መቋጨቱን ተከትሎ፣ ሀገራችንን ጨምሮ በበርካታ የዓለም ሀገራት ቁጥራቸው በሚፈለገው ልክ ባይሆንም የሰላምን ሁለንተናዊ ፋይዳና አስፈላጊነት በሚመለከት የሚያስተምሩ፣የሚጽፉና ጊዜያቸውን ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ አሁንም ሰጥተው የሚወተውቱ ግለሰቦችና ገለልተኛ ተቋማት እንዳሉ ይታወቃል።

በዓለም ላይ እንደ አብነት ከሚጠቀሱ ስለ-ሰላም የበኩላቸውን የላቀ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ግለሰቦች መካከል በፈረንጆች 1867 ፤ልዩ ልዩ ጦር መሳሪያዎችንና የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦችን ለመስራት የሚያገለግል ዳይናማይት የተባለ ንጥረ ነገርን ጨምሮ በርካታ የሳይንስና ምርምር የተዋጣላቸው ሥራዎችን ለዓለም ያበረከተው አልፈርድ በርንሃርድ ኖቤል አንዱ ነው። ይህ የሲውዲን ዜግነት ያለው የኬሚካል ምንድስና ጠበብት፤ እሱ ለዓለም ባበረከተው ንጥረ ነገር በተሰራ የጦር መሳሪያ፤ በዓለም ላይ በተደረጉ ግጭቶች ሳቢያ ላጋጠመ የሰው ሕይወት ጥፋት፣የአካል ጉዳትና የንብረት ወድመት ሁሉ ከልብ በመጸጸት ብዙሃንን የሚያስተምር ልዩ ልዩ የካሳ እርምጃዎችን ወስዷል።

ከነዚህም እርሱ ደረጃ በደረጃ ከወሰዳቸው የማካካሻ ርምጃዎች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት ዕድሜ ዘመኑን በሙሉ ልዩ ልዩ የጤና ዕክል የገጠማቸው 355 ሕሙማን ግዜና የሚያስፈልጋቸውን አሟልቶ መንከባከብን ጨምሮ አጠቃላይ ዳይናማይት ከተሰኘው ንጥረ ነገር ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ በዓለም ላይ በሁሉም ረገድ ሰላም እንዲሰፍን፤ ልዩ ልዩ ስኬታማ አስተዋጽኦዎችን እያበረከቱ የሚገኙ ግለሰቦችን ለማበረታታት የሚያስችል የኖቤል ሽልማት የተሰኘ ድርጅት መመስረት ችሏል።

ሲውዲናዊው አልፈርድ እንደ ግለሰብ ለሚገኝበት የአውሮፓ አህጉር ፣ለሚኖርበት አካባቢና ሀገር ፣ ቀጠናና ዓለም ሁለንተናዊ ሰላም መረጋገጥ የበደል ካሳን ጨምሮ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ጨርሶ በማሟላትና ተገቢ የሰላም ዋጋዎችን ከጥቅም ስሌት በጸዳ መልኩ ጨርሶ መክፈል የቻለ የድርሻውን ማኅበራዊ ኃላፊነት መወጣት እንደሚችል በተግባር ሆኖ ያሳየ የዘመኑ ጀግና የሰላም አምባሳደርም ጭምር ነበር። ኬሚስቱ አልፈርድ በዓለም ላይ ስለ ሰላም በጎ ተጽዕኗቸውን ያኖሩ የሰላም አምባሳደሮች መታየት መንስኤ የነበረ፤ አሁንም ምሳሌነቱ ከመቃብር-በላይ ከፍ ብሎ የሚነገርለት እንደመሆኑ ሁሉ ስለሀገራችን ሰላም መሆን ከአርአያነቱ ልንማር የተገባን ምሳሌ የሚሆን የላቀ አስተሳሰብና ስብዕና ባለቤትም ነው።

በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተውን ጦርነት አላስፈላጊነት በመረዳት ኢትዮጵያውያን ወደ ራሳቸው ወደ ውስጥ ተመልክተው፤ የፖለቲካ ልዩነቶቻቸውን በአፍሪካ ኅብረት ማዕቀፍ ውስጥ ለመፍታት ደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተጓዙ መሆናቸውም እንዲሁ አይዘነጋም። "ልዩነቶችን በሰለጠነ ንግግር መፍታት የምንችል እኛም የአባቶቻችን ልጆች ነን" በሚል መርህ ፤ ለሰላም መቼም ረፍዶ አያውቅምና ደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ላይ ለአፍሪካዊ መፍትሔ ቅድሚያ በሰጠ መልኩ በሰላማዊ ንግግር ችግሩን መፍታት መቻሉ የቅርብ ግዜ ትውስታችንም ጨምር ነው።

የሰላም ድርድሩን እዚሁ በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር በተሳካ ሁኔታ መቋጨት መቻሉ ፤በአፍሪካውያን ዘንድ ለአህጉሩ ሁሉን አቀፍ ችግሮች፤ አህጉራዊ መፍትሔ ማመንጨት የሚቻል መሆኑን ጨምሮ በመሰል የጦርነት አዙሪት ውስጥ እያለፉ ላሉ ሀገራት በቂ ትምህርት የሚሰጥና ምሳሌ በሚሆን መልኩ የተደረገ መሆኑም በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በተለየ ትኩረት በወቅቱ እንዲዘገብ አድርጎታል።

ኢትዮጵያውያን ዓድዋ ላይ ዘምተው ጣሊያንን ድል ማድረጋቸውን ተከትሎ ኢትዮጵያኒዝም የሚል ስያሜ በሰጡት የፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል በርካታ የአፍሪካ ሀገራት፤ እንደ ጎርጎሮሳዊያኑ የዘመን አቆጣጠር በ1960 ነጻ መውጣት መቻላቸውን የዓለም ታሪክ ያስረዳል። አሁን በምንገኝበት ወቅት የአፍሪካ ኅብረት በፈረንጆች 2063 ፣የጥይት ድምጽ የማይሰማበትን አፍሪካ መፍጠር እንዲቻል በአህጉር ደረጃ ይፋ የተደረገውን ግብ ለማሳካት እንዲቻል፤ ኢትዮጵያውያን በፕሪቶሪያ ልዩነቶቻቸውን በእውነተኛ ወንድማማችነት ላይ መሰረት አድርገው የፈቱበት መንገድ በተጨባጭ ልምድና ተሞክሮ የሚሆን ነው በበርካቶች እየተባለም ይገኛል።

የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ በፕሪቶሪያ ከሕወሓት ጋር ያደረገውን ፍሬያማ የሰላም ንግግር ተከትሎ፤ ኦነግ ሸኔ ተብሎ ከሚጠራው ኃይል ጋር ተመሳሳይ የሰላም ንግግሮችን በታንዛኒያ ማስጀመሩም ይታወሳል። ሁለቱም ጥረቶች ለዘላቂ ሰላም መረጋገጥ መንግሥት የድርሻውን ኃላፊነት በተጨባጭ እየተወጣ የሚገኝ መሆኑን የሚያመላክቱም ናቸው!

እንደ መውጫ

በሀገራዊ ምክክርና የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን አማካኝነት፤ ብሔራዊ ምክክር በሚያሻቸው አጀንዳዎች ሁሉ ላይ መክሮ የማያሻማ ውሳኔ ማስተላለፍ መቻል፤ የሀገሪቱን የወደፊት በየደረጃው የሚገለጽ ሁለንተናዊ ዕድገትን ጨምሮ በምትገኝበት ቀጠናና አህጉር እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጽዕኖዋ በሚፈለገው ልክ መጎልበት እንዲችል ፋይዳው የላቀ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለም ከሀገር አቀፍ ምክክሩ ሂደት የሚገኘው አካታች የመፍትሔ ሀሳብ ለሕዝቦች የጋራ ዕጣ ፋንታ መስመር፣ ለሀገሪቱ የህልውና ቀጣይነት፣ ግዛታዊና የሕዝቦቿ በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ አንድነት መጠበቅ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የላቀ እንደመሆኑ ዜጎች በየአካባቢው የሀገራዊ ምክክር እና የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን አባላት የምክክር ሂደቱን ለማሳለጥ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ያልተቆጠበ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል።

# ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶችን - ለንግዱ ዘርፍ ማነቃቅያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከል ንግድና ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት አንዱ ነው፡፡ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትም የተለያዩ ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ባዛርና ኤግዚቢሽኖችን ያዘጋጃል፡፡ ምክር ቤቱ የንግዱን ማህበረሰብ በማሰባሰብ በሚያዘጋጃቸው ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ የንግድ ትርዒቶች አባላቱ ተሳታፊ በመሆን ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ፣ ገበያ እንዲያፈላልጉና ትስስር እንዲፈጥሩ ያደርጋል። በዚህም የተነቃቃ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲኖር ዕድል ይፈጥራል፡፡

ምክር ቤቱ በዘንድሮ 2016 ዓ.ም ብቻ ሶስት የተለያዩ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽኖችን ሊያዘጋጅ መሰናዳቱን ከሰሞኑ አስታውቋል፡፡ ይህን ባሳወቀበት ወቅት የተገኙት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም እንዳሉት፤ ምክር ቤቱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የንግድ ትርኢቶችን በማዘጋጀትና ሌሎችንም ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ተግባራትን በማከናወን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ዘንድሮም ሶስት የተለያዩ የንግድ ትርዒቶችንና ኤግዚቢሽኖችን በተለያየ ጊዜ ለማካሄድ አስፈላጊውን የዝግጅት ሥራዎች አከናውኗል። ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶችና ኤግዚቢሽኖቹ ግብርናና ምግብ ማቀነባበር፣ ማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶችና ኤግዚቢሽኖችም በሀገሪቱ ያለውን ምርትና አገልግሎት ለማስተዋወቅ፣ ገበያ ለማፈላለግ፣ የቴክኖሎጂ ልውውጥ ለማድረግ፣ የሥራ አጋርነትን ለማጠናከርና ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ጉልህ ሚና ይጫወታሉ ብለዋል፡፡

ምክር ቤቱ ከዛሬ 28 ዓመት ጀምሮ የንግድ ትርዒቶችን ሲያካሄድ መቆየቱን ያስታወሱት ዋና ጸሐፊው፤ ዓለም አቀፍ ስጋት ሆኖ በቆየው የኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ላለፉት ሁለት ዓመታት የንግድ ትርዒቱና ኤግዚቢሽኑ ሳይካሄድ መቆየቱን ገልጸዋል።

ዘንድሮ የሚካሄዱት ሶስት የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽኖች በአዲስ ቻምበር ብራንድ የሆኑ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች ስለመሆናቸው ያመለከቱት ዋና ጸሐፊው፤ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ለሁለት ዓመታት ተቋርጦ ዘንድሮ ለ26ኛ ጊዜ የሚካሄደው የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽን አንደኛው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በማኑፋክቸሪንግ የተለያዩ ዘርፎች እንዲሁም ትኩረቱን በቴክኖሎጂ ዘርፍ ላይ የሚያደርገው ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽን ሁለተኛው መሆኑን አስታውቀው፤ በግብርናና በምግብ ማቀነባበር ዘርፍ የሚደረግ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽን ሶስተኛው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱና ኤግዚቢሽኑ አጠቃላይ ትኩረቱ፤ የንግዱ ማህበረሰብ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ተሳታፊ መሆን እንዲችል ሲሆን፤ ሌላኛው የፈጠራ ሥራን በማበረታታት ልማትን ማቀጣጠልና ማዝለቅ የሚል ተልዕኮ የያዘ ስለመሆኑ አመላክተዋል፡፡ ዓለም ወደ ዲጅታል ኢኮኖሚ እየገባ መሆኑን ጠቅሰው፣ ዲጅታል ኢኮኖሚው በኢትዮጵያም የማይቀር ድልና ፈተናም ጭምር በመሆኑ ምክር ቤቱ ሥራ ፈጠራን ያስፋፋል ብለዋል፡፡

የወጣቶችን የሥራ ፈጠራ ለማበረታታትና ለማሳደግ ምክር ቤቱ የቢዝነስ ማዕከል ማስገንባቱንና ወደ ሥራ ማስገባቱንም ተናግረዋል፡፡ ይህም በፈጠራ ሥራቸው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ መቀየር የሚችሉ ወጣቶች እንዲበረታቱ እንደሚያደርግም ገልጸዋል። በተለይም በቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚዘጋጀው የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽን ሥራ ፈጣሪ የሆኑ ወጣቶችን የሚጋብዝ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡ በዚህም ምክር ቤቱ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት፣ የሥራ እድል ለመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ እድሎችን ለመፍጠር ጭምር እንደሚጠቀም ነው ያስረዱት፡፡

**ምክር ቤቱ በቀጣይ የሚያዘጋጃቸው ሶስት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽኖች የሀገሪቱን የንግድ እንቅስቃሴ ማነቃቃት እንደሚችሉ ታምኖባቸዋል፡፡ ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ኩባንያዎችም በሀገር ውስጥ ያለውን ትልቅ አቅም መረዳት እንዲሁም፣ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የንግዱ ዘርፍ አባላት ጋር የገበያ ትስስር መፍጠርና የልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስችሳቸዋል**

እሳቸው እንዳሉት፤ በግብርናው ዘርፍ የሚዘጋጀው የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽንም ትኩረቱን እሴት ጭመራ በማድረግ በምግብ ማቀነባበር ዘርፍ የኢትዮጵያ የምግብና ምግብ ነክ ምርቶች በንግድ ትርዒቱ የሚተዋወቁበት ይሆናል፡፡

በንግድ ትርዒቱም ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ 100 የሚደርሱ የውጭ ኩባንያዎችም ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ቃል የገቡ ኩባንያዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከልም አንደኛው የቱርክ ኩባንያ ሲሆን፣ ይህ የቱርክ የቢዝነስና የንግድ ማስፋፊያ ተቋም በተለያዩ ዘርፎች ተሳታፊ ይሆናል፡፡ ከቱርክ በተጨማሪም በኢትዮጵያና በአፍሪካ የሚገኙ የቻይና ኩባንያዎችና ሌሎችም ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱና ኤግዚቢሽኑ በሚኖረው የንግድ ልውውጥና የገበያ ትስስር ከመፍጠር ባሻገር የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ማሳየት የሚቻልበት አጋጣሚ እንዳለም ዋና ፀሐፊው ይገልጻሉ፡፡ በዚህም የሀገሪቱን በጎ ነገሮች ማጉላት ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

‹‹ቢዝነስ ያለ ሰላም፤ ሰላምም ያለ ቢዝነስ የሚታሰቡ ጉዳዮች አይደሉም›› ያሉት ዋና ፀሐፊው፤ የሰላም ግንባታን በማጠናከር የቢዝነስ ሥራዎችንና ሥራ ፈጠራን በማሳደግ ሀገሪቷን ከድህነት ማውጣት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ለማንኛውም ሥራና ንግድ አመቺ መሆኗን ጠቅሰው፣ በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽን ለሰላም ትኩረት በመስጠት ንግድ የሚስፋፋበትንና ኢንቨስትመንት የሚጠናከርበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚያስፈ ልግ አስታውቀዋል፡፡ ለዚህም ሚዲያው ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበት ገልጸው፤ ሀገሪቷ የሰላምና የሥራ መፍጠሪያ እንደሆነች ማሳወቅና ማስተላለፍ እንደሚገባ ጭምር አመላክተዋል፡፡

ዋና ፀሐፊው እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት ቢዝነስ ለቢዝነስ የሆኑ ግንኙነቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽኑ ለኢትዮጵያ ፖሊሲ አመንጪዎች ጥሪ የሚቀርብበትም ይሆናል። በየዘርፉ ያሉ ለንግድና ኢንቨስትመንቱ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችንና ከውጭ ምንዛሪ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር የንግዱ ማህበረሰብ የጋራ ውይይት የሚያደርግበት መድረክም ይሆናል፡፡ የውይይት መድረኮቹም አጠቃላይ በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚነሱ ችግሮች ጎልተው የሚሰሙበት፣ ጥሪ የሚቀርብበትና መፍትሔ የሚፈለግበት በመሆኑ የንግዱ ማህበረሰብ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው እንዳስ ታወቁት፤ ንግድና ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትና ማሳደግ የምክር ቤቱ ዋና ሥራ ነው፡፡ የግል ዘርፉን ማገዝና መደገፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወሳኝ ይሆናል፡፡

የንግድ ሥራ በባህሪው ከፍተኛ የሆነ የሰዎችን መቀራረብና መግባባት የሚፈልግ ሥራ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፣ ዓለም አቀፍ ስጋት በነበረው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽን ማካሄድ ሳይቻል መቅረቱን አስታውሰዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለውን ሰላማዊ እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ ምክር ቤቱ ወደ ሥራ በመግባት የንግድ ዘርፉን ለማነቃቃት ዝግጁ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሥራ መሥራት ዋና ዓላማው መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህንን በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንደሚሰራ ይናገራሉ፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት የንግድ እንቅስቃሴው የተገደበ በመሆኑ ዘርፉ አሉታዊ ተጽዕኖ ደርሶበት ቆይቷል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ያም ቢሆን ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ተከስቶ የንግድ እንቅስቃሴው በተዘጋበት፣ ሀገራዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተዳከመበትና የሰላም እጦትና የቢዝነሶች መቀዛቀዝ ባለበት ጊዜ ሁሉ ምክር ቤቱ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል ብለዋል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ቢዝነስና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለበርካታ ሀገራዊ ችግሮቻችን መፍትሔዎች በመሆናቸው እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በቀጣይ የሚያዘጋጃቸው ሶስት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽኖች የሀገሪቱን የንግድ እንቅስቃሴ ማነቃቃት እንደሚችሉ ያላቸውን ዕምነት የገለጹት ወይዘሮ መሰንበት፤ ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ኩባንያዎችም በሀገር ውስጥ ያለውን ትልቅ አቅም መረዳት የሚያስችላቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በተያያዘም ከተለያዩ ሀገራት መጥተው በንግድ ትርዒቱ የሚሳተፉ አባላት በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የንግዱ ዘርፍ አባላት ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠርና የልምድ ልውውጥ በማድረግ በሌላው ዓለም ያለው የንግድ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል መረዳት የሚያስችላቸው መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ወይዘሮ መሰንበት እንዳሉት፤ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላቱ ከሌላው የዓለም ክፍል ጋር እኩል ተወዳድሮ መሥራትና የንግድ ልውውጥ ማምጣት የሚችልበትን መንገድ ለማመቻቸት ይሠራሉ፡፡ አባላቱ በወጪና ገቢ ንግድ እንዴት አድርጎ መሥራት እንዳለበት ጭምር ያግዛሉ፡፡ በተለይም ዓለም አቀፍ በሆኑ የንግድ ትርዒቶች ላይ የልምድና የዕውቀት ሽግግር በማድረግ ብዙ የሚማሩበት ዕድል ይፈጠራል፡፡ በንግዱ ማህበረሰብ የሚስተዋሉ የዕውቀት፣ የግንዛቤና ሌሎች ችግሮችንም እንዲሁ ለመፍታት ተቀራርቦ መሥራት ያስፈልጋል፤ በተለይም መሰል ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል፡፡

በሀገር ውስጥ ያለው አብዛኛው የንግዱ ማህበረሰብ በተለይም በወጪ ገቢ ንግዱ ትልቅ ፈተና ያለበት መሆኑን ያመለከቱት ወይዘሮ መሰንበት፤ አንደኛ ምርቱን የሚቀበለው ሰው ማን እንደሆነ እንዲሁም እንዴት መግባባት እንዳለበት ጭምር አያውቅም ብለዋል፡፡ በመሆኑም በርካቶች የተሻለ ጥራት ያለው ምርት አምርተው ለውጭ ገበያ ማቅረብ ሳይችሉ የሚቀሩበት አጋጣሚ እንደሚስተዋል ይጠቅሳሉ፡፡ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ባለፈ የገበያ ትስስር መፍጠር የሚቻለው ዓለም አቀፍ ትላልቅ የንግድ ትርዒቶችን ማዘጋጀት ሲቻል እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በቀጣይ በ2016 ዓ.ም የሚዘጋጁት የንግድ ትርኢቶች ምርትና አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ፣ ገበያ ለማፈላለግ፣ የቴክኖሎጂ ልውውጥ ለማድረግ፣ የሥራ አጋርነትን ለማጠናከርና ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ስለዚህ የንግዱ ማህበረሰብ በእነዚህ የንግድ ትርኢቶች ላይ በንቃት በመሳተፍ የሚፈጠሩ እድሎችን አሟጠው መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

ምክር ቤቱ ዘንድሮ የሚያካሂዳቸው ሶስት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች 26ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ ንግድና ትርኢት፣ 14ኛው የግብርናና ምግብ ንግድ ትርኢትና 6ኛው የማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ የንግድ ትርኢቶች ናቸው፡፡ እነዚህን የንግድ ትርዒቶች ለማዘጋጀት ዝግጅቱን አጠናቅቋል። የግብርናና ምግብ ንግድ ትርኢት ከኅዳር 27 እስከ ኅዳር 29 ቀን 2016 ዓ.ም፤ አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ ንግድ ትርኢት ከየካቲት 14 እስከ የካቲት 18 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲሁም የማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ ንግድ ትርኢት ከግንቦት 15 እስከ ግንቦት 19 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚካሄዱ ጠቁሟል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## «ይቺ ናት ኢትዮጵያ!»

**ክፍል 2**

**ዋለልኝ አየለ**

ከሁለት ሳምንት በፊት መስከረም 2 ቀን 2016 ዓ.ም «ይቺ ናት ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ስለኢትዮጵያ የተፈጥሮ ብዝሃነት አስገራሚነት ማስነበባችን ይታወሳል። በአንድ ወር ውስጥ፣ በአንድ ሳምንት ውስጥ፣ በአንድ ሰዓትና ደቂቃ ውስጥ፤ በአጠቃላይ በአንድ ቅጽበት ውስጥ እንደ ሰሜን ተራሮች ዓይነት በረዶ ያዘለ ቅዝቃዜ እና እንደ ዳሎል ያለ እሳት የሚተፋ ሙቀት ያለባት ናት ኢትዮጵያ!

ይህ በተፈጥሮ የተገኘ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብዝሃነት ግን በማህበራዊ ሕይወትም እንደዚሁ ነው፡፡ ሰሜኑ ከደቡብ፣ ምዕራቡ ከምሥራቅ የተለያየ ዓይነት ሰዋዊ ጥበባት የሚገኙበት ነው፡፡ የተለያዩ ባህልና ወጎች፣ ሃይማኖቶች የሚገኙበት ነው፡፡ በአንድ ትዕይንት ውስጥ ብዙ ነገሮች የሚታዩበት ነው፡፡ ለሥራ ከአንዱ አካባቢ ወደሌላ አካባቢ የሄደ ሰው ሌላ ሀገር ጎብኝቶ እንደመምጣት ነው፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ የብዙ ሀገር ሀብቶች ማለት ነው፡፡

ዛሬ መስከረም 16 ነው፡፡ ይህ ቀን በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የደመራ በዓል ነው፡፡ እነሆ ዘንድሮ ደግሞ ሁለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች እስልምና እና ክርስትና አንድ ቀን በዓል የሚያከብሩበት ቀን ተገጣጠመ፡፡ ዛሬ በእስልምና እምነት ተከታዮች የሚከበረው በዓል መውሊድ ነው፡፡ ሁለቱ ሃይማኖቶች የአንዱ በዓል ለአንደኛውም በዓል ነበር፤ ዘንድሮ ግን አንድ ቀን ተገጣጥሟል፤ እንዲህ አይነት አጋጣሚዎችን ነው «ይቺ ናት ኢትዮጵያ!» ሲባል የምንሰማው፡፡

በቅርቡ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አንድ ምሁር ማብራሪያ ሲሰጡ አሳዘኑኝ፡፡ ምሁሩ ስለኢትዮጵያ ብዝሃነት እያብራሩ ነው፡፡ የሚያብራሩትን ነገር ሲያስቡት በፖለቲከኞች በተደጋጋሚ የሚባል ነገር ሆኖባቸዋል መሰለኝ፡፡ መረር ብለው እያብራሩ «ይህን የምልህ እንዲያው ዝም ብዬ ለፖለቲካል ኮሬክትነስ (political Correctness) እንደሚባለው አይደለም፤ የምርም ስለሆነ ነው» እያሉ ተናገሩ፡፡

ሰውዬው ያሳዘኑብኝ ምክንያት ስሜታቸውን ስለተረዳኋቸውና ስለተጋረኋቸው ነው፡፡ ብሔርን ከብሔር፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት የሚያበጣብጡት ሁሉ ለፖለቲካ ትክክለኝነት (political Correctness) ይጠቀሙታል፡፡ ለፖለቲካ ብልጠት ሲባል መደጋገሙ ነገርዬውን አቀለለው፡፡ ስለብዝሃነት የሚወራው በብዛት በፖለቲከኞች ስለሆነ ብዙ ሰዎች እንደ ፖለቲካ ቃል አዩት፡፡ ምናልባትም አንዳንድ ሰዎች የፖለቲካ ቃል ይመስልብኛል በሚል ለመናገር ይፈሩት ይሆናል፤ ነገርዬው ግን ተፈጥሯዊ ነው፤ የኢትዮጵያ ትክክለኛ ምንነትና ማንነት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚታይና ተጨባጭ የሆነ ሀቅ ነው፡፡ ተፈጥሯዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ብቻ እናስተውል፡፡

ከአለባበስና አመጋገብ ጀምሮ የአንዱን አካባቢ የኢትዮጵያ ክፍል ከሌላው አካባቢ ጋር ማነፃፀር ይቻላል፡፡ ሁለቱን ትልልቅ ሃይማኖቶች ክርስትና እና እስልምና ማየት ይቻላል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ነገሮች ካየን እንደ ኢትዮጵያ ብዝሃነት ያለበት ሀገር ያለ አይመስልም። የተዋሃደ ብዝሃነት ማለት ነው፡፡ ይህ የተዋሃደ ብዝሃነት በውርርስ ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ ይሄዳል፤ ከዚያም ተወዳጅ ይሆናል፡፡ ይህ ብዝሃነት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀገሩን እንዲወድ ያደርጋል፤ ምክንያቱም አዳዲስ የሆነ ነገር ያያል ማለት ነው፡፡ የራሱ ሀገር ብዙ አስደናቂ ነገሮች አሉት ማለት ነው፡፡

ከስድስት ዓመታት በፊት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ጋር ባዘጋጁት አንድ የባህል መድረክ ላይ ታድሜ ነበር፡፡ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የውይይት መነሻ ጽሑፍ ሲያቀርቡ የተናገሩት ነገር በየአጋጣሚው ትዝ ይለኛል። ሃሳባቸው ሲጠቃለል፤ አንድ ሀገር አንድ ዓይነት ነገር ካለው ማንም አይጎበኘውም የሚል ነበር፡፡ በሌላ በኩል አውሮፓውያኑን ለመምሰል የራስን ባህል መበረዝ ማንም እንዳያየው ማድረግ ነው የሚል ነበር። ምክንያቱም የሌላ ሀገር ጎብኚ የሚመጣው አዲስ ነገር ለማየት እንጂ ከራሱ ሀገር ያለውን ነገር ለማየት አይደለም፡፡ ከአውሮፓ ሀገራት አንዱ የመጣ ጎብኚ ወደ ኢትዮጵያ መጣ እንበል፡፡ ኢትዮጵያ ሲመጣ የሚያየው ነገር ሁሉ የራሱ ሀገር አለባበስ፣ የራሱ ሀገር አጨፋፈርና የራሱ ሀገር አመጋገብ ከሆነ ምንም አልጎበኘም ማለት ነው፡፡ በራሱ ሀገር የሰለቸውን ነገር እየደገምንለት ነው ማለት ነው፡፡

ይህን ብዝሃነት ልናስጠብቀው የሚገባ ከውጭ ጎብኚ አንፃር አይደለም፡፡ ከራሳችን አንፃር ነው፤ ለራሳችንም ውበት ስለሆነ ነው፡፡ የዳሸን እና የዳሎል ልዩነት ያስደመሙኝን ያህል ዙምባራ እና እስክስታም ስለሚያስደምሙኝ ነው፡፡ ምንም እንኳን የእምነቱ ተከታይ የበለጠ በጉጉት እንደሚጠብቀው ግልጽ ቢሆንም፤ የእስልምናውም ሆነ የክርስትናው በዓላት የአንዱ ለሌላው በጉጉት የሚጠብቁት ነው። ከምግብ ጋር ለተያያዘው ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ ማህበራዊ መስተጋብሩ ያስገድዳቸዋል፡፡ ልጅ እያለሁ ያስተዋልኩትን ልጥቀስ፡፡

በአካባቢያችን ሙስሊሞች ነበሩ፡፡ በአካባቢው የማህበራዊ ሕይወት ልማድ መሠረት ሠርግ ወይም የዓመት በዓል ሲያጋጥም መተጋገዝ የተለመደ ነው። ሰዎች ደግነታቸውን፣ ሙያቸውን፣ ውለታ ከፋይ መሆናቸውን... የሚያሳዩበት ነው፡፡ አንድ ክርስቲያን ሠርግ ሲያደርግ ለሙስሊሞች ለብቻ በሬ ወይም ፍየል ወይም በግ ይገዛል፡፡ ይህ የሚሆነው ራሳቸው ማረድ ስላለባቸው ነው፡፡ ይህን የሚያደርገው የቀበሌውን ሊቀመንበር ፈርቶ አይደለም፤ ወይም ለማንም አድርባይ ለመሆን ብሎ አይደለም፡፡ ከእነዚያ በክፉ በደጉ ጊዜ አብረውት ከኖሩ ሙስሊም ጎረቤቶቹ መለየት ስለማይችል ነው፡፡

ሙስሊም ሠርግ ሲያድርግ ወይም ሌላ የዓመት በዓል ሲሆንም እንደዚሁ ነው፡፡ ለክርስቲያኖች ለብቻ በሬ ይገዛል፡፡ እኔ ባደኩበት አካባቢ ክርስቲያን ይበዛል። ከሩቅ አካባቢ ካልተጠራ በስተቀር በቅርብ ያሉት ሙስሊሞች የአንድ መንደር ብቻ ናቸው፡፡ ክርስቲያኑ በጣም ብዙ ስለሆነ ብዙ ጊዜ ሙስሊሞች ሠርግ ሲያደርጉ ለክርስቲያኑ በሬ ነው የሚገዙ፤ የሚያርዱትም ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ ክርስቲያን ሠርግ ሲያደርግ ግን እንደ ግለሰቡ አቅም ይወሰናል፡፡ ከሩቅ ያሉትን መጥራት የማይችል ከሆነ ቅርብ ያሉት ሙስሊሞች የአንድ መንደር ብቻ ስለሆኑ የፍየል ሙክት ይገዛል፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ የሚገርሙኝ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ገና ምን እንደሚገዛ ሳያውቁት አስቀድመው «አደራህን ለአንድ ቤተሰብ ብለህ ከብት እንዳታበላሽ፤ ፍየል ይበቃል» እያሉ ሰውዬውን (ባለጉዳዩን) ያስጠነቅቁታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በምክክር ሁሉ ያደርጉታል፡፡

የሃይማኖትን ልዩነት ሳይለቁ በዚህ ልክ አንድ መሆን አይገርምም? እነዚህ ሰዎች ስለልዩነት አያቁም ቢባል «የተማረ» የሚባለው ፖለቲከኛ ያምን ይሆን? ለእነዚህ ሰዎች ስለአንድነት ማስተማር ለቀባሪ ማርዳት አይሆንም?

«ይቺ ናት ኢትዮጵያ!» ሲባል ትዝ የሚሉኝ እነዚህ በአካባቢዬ ያየኋቸው ማህበረሰባዊ አብሮነቶች ናቸው፡፡ ትዝ የሚለኝ ለመስቀል በዓል የተጣላ ጎረቤት የሚያስታርቀው ሙስሊሙ ጋሼ አሕመድ ነው፡፡ ትዝ የሚለኝ የሮመዳን ጾም ሲገባ ፀሐይ ሲመታቸው ውሃ ይጠማቸዋል በሚል ክርስቲያኖች የሙስሊሞችን ጤፍ ሲያጭዱላቸው ነው፡፡ ታዲያ ይህ «ይቺ ናት ኢትዮጵያ!» አያስብልም?

**ለሙስሊሙም ለኦርቶዶክሱም መልካም በዓል!**

# ዓለም አቀፍ

## ግብጽን ለመደገፍ ጉቦ በመቀበል የተከሰሱት አሜሪካዊ የምክር ቤት አባል ክሱን አስተባበሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የግብጽ መንግሥትን ለመደገፍ ጉቦ ተቀብለዋል ተብለው የተከሰሱት የአሜሪካ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ቦብ ሜንዴዝ ከወንጀሉ ነጻ ነኝ ሲሉ ተናገሩ።

በቤታቸው በፍተሻ የተገኘው ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ ዶላር ለአስርት ዓመታት የለፉበት ገንዘብ እንደሆነም ገልጸዋል።

ቤታቸው ውስጥ ይህን ያህል ገንዘብ ያስቀመጡትም በባለሥልጣናት ሊወሰድ ይችላል በሚል ከኩባ ወላጆቻቸው በተላለፈባቸው ስጋት መሆኑንም አስረድተዋል።

የኒውጀርሲው ተወካይ ሮበርት ሜንዴዝ ከሙስና ክስ ነጻ መውጣት ብቻ ሳይሆን በሚቀጥለው ዓመት በምርጫ እንደሚወዳደሩም ተናግረዋል።



የአሜሪካ የፍትህ ሚኒስቴር ፖለቲከኛውና ባለቤታቸው የግብጽ መንግሥትን ለመደገፍ በሙቶ ሺዎች የሚቆጠር ዶላር ጉቦ ተቀብለዋል ሲል ከሷል።

ባለፈው ሳምንት ዓርብ ዕለት ይፋ በሆነው ባለ 39 ገጾች ክስ መሠረት ሜንዴዝ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በሀገራቸው እና በውጭ ሀገራት ባሉ የሙስና እቅዶች ላይ ተጽእኖ በማሳደር ክስ ቀርቦባቸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሊቀ መንበር በአሜሪካ በሚገኘው የግብጽ ኤምባሲ ውስጥ የሚሰሩ ዲፕሎማቶችን በተመለከተ ከፍተኛ ምስጢራዊ መረጃዎችን በማጋራት እንዲሁም የግብጽን መንግሥት ምስጢራዊ በሆነ ሁኔታ የሚደግፉ ርምጃዎችን ወስደዋል ተብለዋል።

ለዚህም ሜንዴዝና ባለቤታቸው ናዲን አርስላኒያን ከሦስት የኒውጀርሲ ነጋዴዎች ገንዘብ፣ ወርቅ፣ ለቤት ብድር የተፈጸመ ክፍያና የቅንጦት ተሽከርካሪ ጉቦ እንደተቀበሉም ክሱ ያስረዳል።

የቋሚ ኮሚቴው ሊቀመንበር በትውልድ ሀገራቸው ኒውጀርሲ ከሚገኙ ዲሞክራቶች ከአባልነታቸው እንዲለቁ የቀረበላቸውን ጥያቄም ውድቅ አድርገዋል።

"ሁሉም እውነታዎች ግልጽ ሲሆኑ ከወንጀሉ ነጻ መሆን ብቻ ሳይሆን አሁንም በኒውጀርሲ ከፍተኛ የምክር ቤት አባልነቴ እቀጥላለሁ" ሲሉም ሜንዴዝ ሰኞ እለት በነበረው ጋዜጣዊ መግለጫ ተናግረዋል።

ፖለቲከኛው ባለፈው ሳምንት ዓርብ ከተከሰሱ ጀምሮ በአደባባይ ላይ ሲታዩ ይህ የመጀመሪያቸው ነው።

"በኔ ላይ ለመፍረድ የተጣደፋችሁ አቃቤ ሕግ በሰጣችሁና ሆን ተብለው በተወሰኑ መረጃዎች ላይ ተመስርታችሁ ነው።" ብለዋል።

ባለፈው ዓመት የፌደራል የደኅንነት ሠራተኞች የፖለቲከኛውን ቤት በፈተሹበት ወቅት ከ480 ሺህ ዶላር በላይ በጥሬ ገንዘብ በአብዛኛው በፖስታ ውስጥ እንዲሁም በልብስ ውስጥ ኪሶች፣ በቁም ሳጥኖች እና ካዝናዎች ውስጥ ተደብቀው መገኘታቸውም ተገልጿል።

ሰኞ ዕለት በነበራቸው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ "ከግል ቁጠባ አካውንቴ በሺዎች የሚቆጠር ዶላር በጥሬ ገንዘብ አውጥቻለሁ። ይህንን ገንዘብ ቤት ያስቀመጥኩት ለድንገተኛ አደጋ እና ወላጆቼ ኩባ በነበሩበት ወቅት በባለሥልጣናት ገንዘባቸው ከመወረሱ ጋር ተያይዞ ያደረብኝ ስጋት ነው።" ሲሉም ነው የተናገሩት።

## ሊቢያ ከጎርፍ አደጋው ጋር በተያያዘ የዴርና ከተማ ከንቲባን አሰረች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በከፍተኛ ጎርፍ ተጥለቅልቃ አሰቃቂ አደጋ ያስተናገደችው የሊቢያዋ ከተማ ዴርና ከንቲባ ከክስተቱ ጋር በተገናኘ መታሰራቸውን ታውቋል።

አብዱልመናን አል ጋሃኣቲ የተባሉት ከንቲባ ከሳምንታት በበፊት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በተቀጠፉበት የጎርፍ አደጋ ምክንያት ክስ ከተመሰረተባቸው በርካታ የመንግሥት ባለስልጣናት አንዱ ናቸው።

ባለፈው ሳምንት በክስተቱ የተቆጡ የዴርና ከተማ ነዋሪዎች ባደረጉት ተቃውሞ የከንቲባውን ቤት እሳት ለቀውበታል።

በትሪፖሊ የሚገኘው የሀገሪቱ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ትላንት ባወጣው መግለጫ ባለስልጣናቱ በጎርፍ የፈረሰውን "የአካባቢውን ግድብ መሠረተ ልማት የማስተዳደር ኃላፊነት ነበረባቸው" ብሏል።

በዚህም ሳቢያ የወንጀል ክስ እንደከፈተባቸው ጠቅሷል። ከንቲባ አል አል ጋሃኣቲን ጨምሮ የተወሰኑ ባለሥልጣናት ከፍርድ ሂደቱ ቀደም ብሎ ታስረዋል።

የጠቅላይ አቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤቱ በመግለጫው በዴርና ከተማ ከፍተኛ ጎርፍ እንዲከሰት ምክንያት ለሆነው የግድቡ መፍረስ ተጠያቂ ያደረገ ሲሆን ግድቡን ለመጠገን የቀረበውን ገንዘብ ተገቢ ባልሆነ መንገድ አስተዳድረዋል ብሏል።

የከንቲባው ጽሕፈት ቤትም ከጎርፍ ጋር በተያያዘ በርካቶች እንዲሞቱና ሊቢያም የኢኮኖሚ ኪሳራ



እንዲገጥማት ባደረገው አደጋ ባለሥልጣናት ቀድመው ርምጃ ለመውሰድ ቸልተኛ ሆነዋል ብሏል።

ከንቲባ አብዱልመናን አል ጋሃኣቲ ሥልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ሌላ ክስ እንደሚጠብቃቸውም ተነግሯል። ሊቢያ በምሥራቅና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ ተቀናቃኝ ኃይሎች አስተዳደር ስር የምትገኝ ሀገር ናት።

በትሪፖሊ የሚገኘው ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የምዕራብ የሀገሪቱን ክፍል እንደመያዙ በምሥራቁ ያሉ ተጠርጣሪዎች ለመያዝ ትዕዛዝ ምን ያህል ርቀት እንደሚጓዝ ግልጽ አይደለም።

ባለፈው እሁድ የምሥራቁ የሀገሪቱ መንግሥት በጎርፍ አደጋው እንደሞቱ የተረጋገጡ ሰዎች ቁጥር 3 ሺህ 868 መደረሱን ገልጿል።

የጠቅላይ አቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ከአደጋው ጋር በተያያዘ እየተደረገ ያለው ምርምራ እንደቀጠለ ገልጾ ሌሎች ተጨማሪ የሚታሰሩ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አመላክቷል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ደጃዝማች ዑመር ሰመተር -የኦጋዴኑ የበረሃው መብረቅ

ከዓድዋ ድል ማግስት ኢትዮጵያ የግዛት ማስፋፋት ልታስብ ትችላለች በሚል የብዙ ቅኝ ገዥ ሀገራትን ትኩረት ስባ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ በሰሜንና በደቡብ ምስራቅ ጣሊያን፣ በደቡብ ምዕራብ እንግሊዝ እንዲሁም በምስራቅ ፈረንሳይ እንደከበባ ያለ አካሄድ ቃጥቷቸው ነበር፡፡

የድንበር የውል ስምምነቶችን ወደ ጠረጴዛ ለማምጣት መሞከር ጣሊያን ለረጅም ጊዜ የሰራችው ኢትዮጵያን የመያዣና ለበቀል የሚሆን ጊዜ የማመቻቸት ሥራዎች መካከል ይጠቀሳል፡፡ ለዚህ አብነት የሚሆነው ጣሊያን በቅኝ በያዘቻት የያን ጊዜዋ የጣሊያን ሶማሌላንድና በኢትዮጵያ መንግሥት በ1900 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት ነው፡፡

ጣሊያን በዓድዋ የገጠማትን ሽንፈት ቁስል በድል ለመሻር ሀገሪቱን ለመምራት ወደ ስልጣን የመጡት ሁሉ እያሰቡና እየተመኙ ዓመታት ቢያልፉም በ1922 ወደ ስልጣን የመጣው ሞሶሎኒ ተንኮል በመፈለግ እረፍት እንዳልነበረው ይጠቀሳል፡፡በሐረር የኦጋዴን አውራጃ የወልወል ወረራም በዚሁ ስሜት የተወለደ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል።

በኅዳር ወር 1927 ዓ.ም ለወልወል ግጭት በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል በተደረገ የድንበር ስምምነት ስምምነቱን ለማስተግበር ወደ ስፍራው የሄዱ ኮሚሽነሮች ቦታው ላይ ሲደርሱ የጣሊያን ወታደሮች ቀድመው የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው በማግኘታቸው ለቀናት በፍጥጫ ከቆዩ በኋላ ወደ ጦርነት አምርተዋል፡፡

ወልወል የኢትዮጵያ ይዞታ ብትሆንም በመንግሥቱ የጥበቃ መዳከም ተጠቅማ የሰፈረችው ጣሊያን በተለያየ መንገድ ኢትዮጵያ ላይ ተፅእኖ ማሳደሯን ቀጥላ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የተፈጠረው መካረርም ወደ ጦር መማዘዝ እንዲያድግና የዓድዋን የሽንፈት ካባ አውልቃ ኢትዮጵያን ድል ነስታ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ያጣችውን ክብር ለመመለስ አጋጣሚውን እንደ መንደርደሪያም ተጠቅማበታለች።

ከሮም የተላከው የጣሊያን ጦር መስከረም 22 ቀን 1928 የመረብን ወንዝ ተሻግሮ በዓድዋ፣ በአዲግራት ጦርነት ከፍቶ ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያን አርበኞችና መሪዎችም ዓለም የጣሊያንን ወራሪነት እንዲያይና በከበባ ትጥቁን እንዲሁም ስንቁን ለማስጨረስ በማሰብ ጦሩ ምንም ዓይነት ችግር ሳይገጥመው ወደ መሀል ሀገር እንዲገባ ፈቀዱ፡፡

በ9 ክፍለ ጦሮች ተዘጋጅቶ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የጣሊያን ጦር ቤታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ እርሻቸውን ሁሉ ትተው ጫካ በገቡ ኢትዮጵያውያን አርበኞች እረፍት እያጣም ቢሆን ለአምስት ዓመታት ቆይታ አድርጓል፡፡ ኢትዮጵያውያን የመንፈስና የአካል ጉዳት አቅም ሊያሳጣቸው ቢሞክርም ጠላትን እምቢ በማለት ዓድዋ ላይ ድል ያደረጉ አባቶችን ታሪክ በመድገም ከአምስት ዓመታት ትግል በኋላ ሀገራቸውን ከፋሽስት ነጻ አውጥተዋል፡፡

በ1928 ዓ.ም ፋሽስት ጣሊያን ሀገራችንን በወረራ ወቅት በርካታ ኢትዮጵያውያን ለሀገር ክብር ሲሉ በተለያየ አውደ ውጊያዎች ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ ሀገር በጠላት በተወረረ ወቅት ሕዝቡ ቀፎው እንደተነካ ንብ ከየአቅጣጫው በመትመም ጠላትን ድባቅ ለመምታት ዘምቷል፡፡ በወቅቱ የነበረው ትውልድ ይህን የአርበኝነት ባህል ከአባቶቹ የዓድዋ ድል የተቀበለውና የወረሰው ነው፡፡ እስከ 1928ቱ የጠላት ወረራ ወቅት ድረስ ጎልቶ ይንጸባረቅ የነበረው የአርበኝነት አስተሳሰብ ‹ማንም ወራሪ ኃይል ቢመጣ እኛ ኢትዮጵያውያንን ማሸነፍ አይችልም» የሚለው ነበር፡፡ ይህ አስተሳሰብ የመነጨው ከታሪካችን ነው፡፡

ከወረራው በፊት የነበረው ታሪካችን የድል እንጂ የሽንፈት አይደለም፡፡ የጣሊያን ፋሽስት ጦር ሀገሪቷን ለአምስት ዓመት በወረረበት ወቅት በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች የአርበኝነት እንቅስቃሴ መካሄዱ ወራሪው ኃይል የተረጋጋ መንግሥት እንዳይመሰረት እንቅፋት ሆነውበታል፡፡ አርበኞቹ የጠላትን እለታዊ እንቅስቃሴ በማወክ፣ ሕዝቡ ተስፋ እንዳይቆርጥና ሀገር ለጠላት እንዳትገዛ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ በወቅቱ የነበረው የፋሽስት ወረራ ከዓድዋው ዘመን የተለየ የሚያደርገው ከጠላት በኩል በጦር ኃይል፣ በፕሮፓጋንዳ፣ በሥነ ልቡና፣ በወታደራዊ ዝግጅት ጠላት ሙሉ ለሙሉ የበላይነት የነበረው መሆኑ ነው፡፡



የኢጣልያ ጦር በወልወል የጫረው እሳት በሰሜን ተያይዞ በነበረበት በዛ ቀውጢ ቀን ሀገር በጣልያን እንዳትወረር በዱር በገደሉ ሲጠባበቁ በነበረበት ወቅት በምሥራቁ ኢትዮጵያ ክፍል ከደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማያት ጋር በመሆን ዑመር ሰመተር የትግሉን ጎራ ተቀላቀሉ

በተቃራኒው ከኢትዮጵያ አንጻር ደግሞ የሀገሪቷ ማዕከላዊ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ በፈረሰበት፣ በዘመናዊና በበቂ የጦር መሳሪያ ያልተደራጀ ሠራዊት የነበረበት፣ ንጉሠ ነገሥቱ የተሰደዱበት ወቅት መሆኑ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ እኛ ኢትዮጵያውያንን ማንም አያሸንፈንም የሚለው ለዘመናት ስር የሰደደ አስተሳሰብና በራስ የመተማመን መንፈሳዊ ጸጋ ፈተና ውስጥ የወደቀበት መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ከባድና ተስፋ አስቆራጭ ወቅት ነበር በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ለሀገር ክብር መስዋዕት ለመክፈል የአርበኝነት እንቅስቃሴ የተደረገው። የአርበኝነቱ እንቅስቃሴ ይደረግ የነበረውም ፍቃደኛ የሆኑ ግለሰቦች በግል የነበራቸውን ኋላቀር ጠመንጃ፣ ሽጉጥ ፣ጦር፣ ጎራዴና ጩቤ በመያዝ ጫካ በመግባት ነበር፡፡

ጣሊያን 40 ዓመታት ያክል ስትዘጋጅ ቆይታ ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም ኢትዮጵያን የወረረች ቢሆንም የኢትዮጵያ አርበኞች በከፈሉት መስዋዕትነት በድጋሚ ድል ማድረግ ተችሏል፡፡ የዚህ ድል ባለቤት ከሆኑትና ለኢትዮጵያ ሕዝብም ባለውለታ ከሆኑ ጀግኖች ውስጥ አንዱ ደጃዝማች ኡመር ሰመተር አንዱ ናቸው፡፡

ደጃዝማች ዑመር ሰመተር በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ለሀገራቸው ነጻነት ሲሉ በፍጹም ሀገራዊ ፍቅር መተኪያ የሌለው ሕይወታቸውን የከፈሉ አካላቸውን ያጎደሉ በርካቶች ናቸው፡፡ የቀደሙትን የእነዚህን አባቶች ውለታ አቅም በፈቀደ በምናስታውስበት በዚህ ገጽ ዛሬ ዕድል ቀናንና ታላቁን ኢትዮጵያዊ ጀግና ደጃዝማች ዑመር ሰመተረን ልንዘክር ተገናኘን..... እነሆ ሰውየው!!!

አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ከታላቁ አንዋር መስጊድ አጠገብ “ዑመር ሰመተረ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት” የሚል መጠሪያ የተሰጠውን ት/ቤት (አሁን ፈርሶ ፓርኪንግ ሆኗል) ሲያስቡ ከታሪኩ በስተጀርባ መታሰቢያ የቆመላቸው እኚህ ሰው ማን ናቸው ብለው መጠየቅዎ ወይም በሌላ ሰው መጠየቅዎ አይቀርም፡፡

የዛሬው ባለታሪካችን የተወለዱት በኦጋዴን አካባቢ ካልካዩ በተባለ ሥፍራ ሲሆን ዓመቱም 1871 ዓ.ም ነው፡፡ በልጅነታቸው የተለያዩ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ባህላዊ ሥርዓቶችን እየተማሩ ያደጉት እኚህ ሰው የአስተዳደር ሰው ለመሆን በነበራቸው ፍላጎት የመሪነት ክህሎታቸውን ሊያሳኩ የሚችሉ የተለያዩ ጥረቶችን እየሚከሩና ከአካባቢው የጎሳ መሪዎች አሰራርና ተሞክሮን እየቀሰሙ ማደጋቸው ይነገራል፡፡ ለአካለ መጠን ሲደርሱም በአካባቢ አስተዳደር ሥራ በመሰማራት ሀገራቸውን ያገለገሉ ሲሆን በቅድሚያ በባላባትነት ማዕረግ በመቀጠልም የሱልጣን ዓሊ የሱፍ እንደራሴ ሆነው በናኢባነት እንደዚሁም የኤል-ቡር ገዢ በመሆን ለ23 ዓመታት ሀገራቸውን በፍጹም ቅንነት አገልግለዋል፡፡

የታሪክ ጠላታችን ፋሺስት ኢጣልያ የዓድዋ ሽንፈቱዋን ለመበቀል ሴራ መጠንሰሱዋን አሀዱ ያለችው በወልወሉ ግጭት ነበር። የወልወል ግጭት መሠረቱ እንዲህ ነው... የእንግሊዝና የኢትዮጵያ መንግሥት በሶማሊያ በኩል ባለው የግዛታቸው ወሰን በደንብ ለመከለል ስምምነት አድርገው ስለነበር ቀን ተቆርጦ ወደሥራ ሲገባ ሥራውን እንዲያከናውኑ ከእንግሊዝ ኮሎኔል ክሊፎርድ ከኢትዮጵያ ወገን ደግሞ ፊታውራሪ ተሰማ ባንቴ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት የወሰን ክልሉን ለማጥናት በተንቀሳቀሱበት ወቅት ካፒቴን ሺማትሩ የተባለ የኢጣልያ ተወላጅ ቀደም ሲል ከደረሰበት የወሰን ስምምነት መቶ ኪሎ ሜትር የሚያህል አልፎ እንደጠብ አጫሪነት መተላለፊያ ከለከለ..... በዚህ ነገር ግራ የተጋቡት የኢትዮጵያ ተወካዮች በሰውየው አድራጎት ላይ ማብራሪያ ለመስማት እንኳን ባላስቻለ ፍጥነት ጦሩን አዝምቶ በአየርና በምድር ጦርነት በመክፈት ያለተዘጋጁትን የኛን ወገኖች አጠቃቸው...... በዚህ ጦርነት ፊታውራሪ ዓለማየሁን ጨምሮ ቁጥራቸው 107 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በክብር ሲወደቁ 75 ያላነሱ የፋሽስት ወታደሮች ሞቱ፡፡

የኢጣልያ ጦር በወልወል የጫረው እሳት በሰሜን ተያይዞ በነበረበት በዛ ቀውጢ ቀን ሀገር በጣልያን እንዳትወረር በዱር በገደሉ ሲጠባበቁ በነበረበት ወቅት በምሥራቁ ኢትዮጵያ ክፍል ከደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማያት ጋር በመሆን ዑመር ሰመተር የትግሉን ጎራ ተቀላቀሉ፡፡ በዚህም ወቅት ከአቻ ወንድሞቹ ጋር በተለያዩ የጦር አውደ ግንባሮች የተሰለፈው የሶማሌ ጦር ጠላትን መውጫ መግቢያ አሳጥቶ የእግር እሳት ሲሆንበት በተለይም ደግሞ በዑመር ሰመተረ የሚመራው ጦር ጎርበሌ ላይ መሸጎ እየወረወረ የጠላት ጦርን መድረሻ አሳጣው በመሪው በኡመር ሰመተር ኢትዮጵያውያን በድል ጎዳና ተራመዱ......አይቀጡ ቅጣት የተቀጣው የጠላት ጦር ሊመሽበት እንደሆነ ተረዳና ከሱው ብሶ ስሞታ ለዓለም መንግሥት አሰማ...... በዚህ ስሞታው ካሳ እንዲከፈለው ብቻ አልጠየቀም ጀግናው ዑመር ሰመተር እንዲሰጠው ጭምር እንጂ........ በተለያዩ የጦር አውደ ግንባሮች ድልን መጎናጸፍ የጀመረው የዑመር ጦር ኤል ቡር ላይ ፋሺስት ቦታውን በስድስት ባታሊዮን ጦር ተከበበ.... እውነታው የገባቸው የጦር አበጋዙ ለጊዜውም ቢሆን ማፈግፈጉን መረጡ... ፋሽስት ድል ያገኘ መሰለው... ይሁንና ለ5 ወራት ያህል ጦራቸውን በማደራጀት የቆዩት ዑመር በ1930 ዓ.ም ሌሊት በጠላት ጦር ላይ ያልታሰበ አደጋ ጣሉ ያንን የተፈራ ባለ ብዙ ባታልዮን ጦር ከጥቅም ውጭ አደረጉት.... በድል እየዘመሩ ለሌላ ጥቃት ሽላቦ ላይ ሰፈሩ..... አሁንም ፋሺስት ሽላቦ ድረስ እየመጣ አላስቀምጥ አላቸው... እንደገና ገጥመው ድል አደረጉት.... በቆራሄም ጠላት አፈረ ከጠላት ምሽግ የጨበጣ ውጊያ በማካሄድ ታላቅ ጀብዱ ፈጸሙ፡፡

የጠላት ጦር ኃይሉ እየከበደ ሲመጣ በጉርለጉቤው ጦርነት ዑመር በጠላት ጥይቶች ተመቱ፡፡ ደጃዝማች ዑመር ሰውነታቸው በስድስት ጥይቶች በመቁሰሉ በጦርነት ለመሳተፍ ከማይችሉበት ደረጃ ደረሱ፡፡ በዚሁ ምክንያት ለሕክምና በቅድሚያ ሀርጌሳ ከዛም በኬንያ በኩል ተጉዘው ወደ ሎንደን ተላኩ፡፡

እስከ ጦርነቱ ማብቂያ በሎንዶን የቆዩት ዑመር ሰመተር ነጻነት ሲመለስ ባንዲራ ሲሰቀል አርበኛው ሁሉ እየፎከረና እያቅራራ ግዳጅ ሲጥል የድል አጥቢ አርበኛውም ለጀግንነቱ ምስክር ሲገዛ ፊታውራሪ ዑመር(በኋላ ደጃዝማች) በኦጋዴን ከጦርነቱ የተረፉትን አርበኞች አክብረው የሚገባቸውን ሸለሟቸው!!!

ታላቁ ጀግናችን ዑመር ሰመተረ የተጣለባቸው የጠላት ጥይት ጤና እየነሳቸው ቁስሉም እየመረቀዘ ስላስቸገራቸው በሐረር ከተማ ሀኪሞች ባሉበት ቦታ ሁሉ እየተዘዋወሩ ቢታከሙም ለመዳን ግን ሳይችሉ ቀረ በተወለዱ በ61 ዓመታቸው መጋቢት 10 ቀን 1936 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ!!!

ሐረር ከተማ በሚገኘው በአብደል መካነ መቃብር መኳንንቶችን አስከትለው ክርስቲያንና እና እስላሙ በነቂስ ወጥቶ ለጀግና በሚሆን በሙሉ ወታደራዊ ክብር ተሸኙ!!!

በዚህ የቀብር ሥነ ሥርዓት አብዶ ሀይድ የተባሉ የትግል ጓዳቸው ይህንን አንጀት የሚበላ ቅኔ ተቀኙላቸው።

**ተገዳይ እወልወል እጠረፉ ዳር፤**

**ተጋዳይ አፍዱግ ሳይ እጠረፉ ዳር፤**

**ተጋዳይ ቆራሄ እጠረፉ ዳር፤**

**ተጋዳይ ሀነሌ እጠረፉ ሳይ፤**

**የመትረየሱ ሼክ የሰበን መምህር፤**

**ሞት ጠራህ አንተንም ዑመር ስመጥር!!!**

**ምንጭ፡**

- **የኢትዮጵያ ታሪክ œ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ**
- **ያልተዘመረላቸው œ በፍጹም ወ/ማርያም**
- **የተለያዩ ድረ ገጾች**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم አል-ዓለም
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ሉሲዎቹ ወደ ቀጣዩ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ማለፍ አልቻሉም

**ቦጋለ አበበ**

ሞሮኮ በ2024 ለተከታታይ ሁለተኛ ጊዜ በምታስተናግደው 14ኛው የሴቶች አፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ የመጀመሪያውን ዙር የማጣሪያ ውድድር ያደረጉት የኢትዮጵያ ሴቶች ብሔራዊ ቡድን(ሉሲዎቹ) ወደ ቀጣዩ ዙር ማለፍ አልቻሉም።

ሉሲዎቹ በማጣሪያ ጨዋታው ቡሩንዲን የገጠሙ ሲሆን፤ የደርሶ መልሱን ጨዋታ በቡሩንዲ ፍቃደኝነት አዲስ አበባ ላይ ነበር ያደረጉት። ይህም ለሉሲዎቹ ጥሩ አጋጣሚ በመሆኑ በደርሶ መልስ ጨዋታ ውጤት ወደ ቀጣዩ ዙር ያልፋሉ ተብሎ እንዲጠበቅ አድርጎ ነበር።

የመጀመሪያውን ጨዋታ በአበበ ቢቂላ ስቴድየም ባለፈው አርብ ያደረጉት ሉሲዎቹ በረድዔት አስረሳኸኝ ግብ መምራት ቢችሉም አንድ ለአንድ ነበር የተለያዩት። ያም ሆኖ በሁለተኛው ጨዋታ ያሸንፋሉ ተብሎ ብዙ ተስፋ ተደርጎ ነበር።

ሁለተኛው የማጣሪያ ጨዋታ ትናንት በተመሳሳይ አበበ ቢቂላ ስቴድየም ሲካሄድ ረድዔት አስረሳኸኝ በ19ኛው ደቂቃ ባስቆጠረችው ግብ ሉሲዎቹ በድምር ውጤት ሁለት ለአንድ መምራት ችለው ነበር። 48ኛው ደቂቃ ላይ ግን ቡሩንዲዎች የአቻነት ግብ በማስቆጠር በማጣሪያ ፉክክሩ መቆየት ችለዋል። ሉሲዎቹ በጨዋታው ተጨማሪ ጎል አስቆጥረው ወደ ቀጣዩ ዙር ለማለፍ በኳስ ቁጥጥር ልቀው የተሻለ እንቅስቃሴ ቢያደርጉም ያገኙትን አጋጣሚ ተጠቅመው ኳስና መረብ ማገናኘት አልቻሉም። በዚህም ውጤት ጨዋታው በመጠናቀቁ ወደ መለያ ምት አምርቶ ቡሩንዲ 5ለ3 በማሸነፍ ወደ ቀጣዩ ዙር ማጣሪያ ማለፏን አረጋግጣለች።



ሉሲዎቹ ከሞሮኮ አፍሪካ ዋንጫ ውጪ መሆናቸውን አረጋግጠዋል

በአሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል የሚመራው የሉሲዎቹ ስብስብ በርካታ ወጣት ተጫዋቾችን ይዞ ከረጅም ዓመት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ለመመለስ ቢዘጋጅም በሜዳውና በደጋፊው ፊት የነበረውን እድል መጠቀም አልቻለም። በዚህም የመጨረሻውን ዙር ማጣሪያ ከወዲሁ ለመሰናበት ተገዷል።

ቡሩንዲ ቀጣዩን ዙር መቀላቀሉን ተከትሎ በመጨረሻው ማጣሪያ ከዩጋንዳና አልጄሪያ አሸናፊ ጋር የምትገናኝ ይሆናል። አልጄሪያ የመጀመሪያውን ጨዋታ ከሜዳዋ ውጪ 2ለ1 አሸንፋለች፣ ይህም በመልሱ ጨዋታ በሜዳዋ አሸንፋ ቡሩንዲን የመግጠም የተሻለ እድል እንዲኖራት አድርጓል።

እኤአ ከ1991 ጀምሮ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን(ካፍ) አዘጋጅነት የሚካሄደው የሴቶች የአፍሪካ ዋንጫ ሀገራት በደርሶ መልስ ጨዋታ እንደ ዓለም ዋንጫ ማጣሪያ የሚያደርጉት ፍልሚያ ነበር። እኤአ ከ1998 ጀምሮ ግን ልክ እንደወንዶቹ የአፍሪካ ዋንጫ ራሱን የቻለ ትልቅ የአህጉሪቱ ውድድር በመሆን በየሁለት ዓመቱ እየተካሄደ ይገኛል።

ሉሲዎቹ በዚህ ትልቅ መድረክ እኤአ ከ2002 ናይጄሪያ ያዘጋጀችው አፍሪካ ዋንጫ የመጀመሪያ ተሳትፏቸውን አድርገዋል። በዚያ ውድድር ከምድብ ጨዋታዎች የዘለለ ውጤት ግን አላስመዘገቡም። እኤአ በ2004 በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት በተካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ ለሁለተኛ ጊዜ ተሳትፈው አራተኛ ሆነው ያጠናቀቁበት ውድድር በታሪካቸው አሁንም ድረስ ትልቁ ውጤት ሆኖ ተመዝግቧል። ከዚህ የተሻለ ውጤት በቀጣይ 2006 ላይ ናይጄሪያ ባዘጋጀችው የአፍሪካ ዋንጫ ያስመዘግባሉ ተብሎ ቢጠበቅም ከማጣሪያ ጨዋታዎች አስቀድሞ በውድድሩ ሳይሳተፉ ቀርተዋል። በ2008ቱ የኢኳቶሪያል ጊኒና በ2010 የደቡብ አፍሪካ ዋንጫ ደግሞ ማጣሪያውን ማለፍ አልቻሉም። በቀጣይ እኤአ 2012 ኢኳቶሪያል ጊኒ ባዘጋጀችው የአፍሪካ ዋንጫ መቅረብ ቢችሉም ከምድብ ጨዋታዎች ማለፍ ሳይችሉ በጊዜ ከውድድሩ ተሰናብተዋል። ከዚያም በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ሳይመለሱ አስራ ሁለት ዓመታት ተቆጥረዋል።

የዛሬው የአሰልጣኝ ፍሬው የወጣቶች ስብስብ ይህን ታሪክ ለመቀየር ከመጀመሪያው ማጣሪያ ከወዲሁ መሰናበቱን ተከትሎ ሉሲዎቹ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ለመመለስ ተጨማሪ ሁለት ዓመታትን ሊጠብቅ ተገዷል።

## ከዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የእንሰት አጠውልግ በሽታና ምርታማነቱ ላይ እያሳደረ ያለው ተጽዕኖ

**ዳንኤል ዘነበ**

የእንሰት ተክል በብዛት ከሚመረትባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች ደቡብ ክልል ቀዳሚ ሲሆን፤ ተክሉ በሀገሪቷ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለምግብ ፍጆታ፣ ተረፈ ምርቱ ለእንስሳት መኖነት፣ ለቤት እና ለተለያዩ ቁሶች መሥሪያነት በግብዓትነት ይገለገሉበታል።ከዚህ ግልጋሎቱ ባለፈ እሴት በመጨመር ለኢንዱስትሪ ምርቶች በግብዓትነት በማዋል እና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የኢትዮጵያን የውጭ ምንዛሪ ግኝት እያሳደጉበትም ነው።

እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አልፎ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የማሳደግ አቅም እንዳለው የተመሰከረለት የእንሰት ተክል ፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተክሉ ላይ እንሰት አጠውልግ የተሰኘ በሽታ በመከሰቱ ምክንያት በምርታማነቱ ላይ ተፅእኖ በማሳደር ቀላል የማይባል ጉዳት እያደረሰ ይገኛል። የአርሶ አደሩ ዋነኛ የምግብ ምንጭ ለሆነው ለእንሰት ሰብል ትኩረት ባለመሰጠቱ እና በቂ ጥናትና ምርምር ባለመካሄዱ ተክሉ ሊጠቃ እንደቻለ የዘርፉ ተመራማሪዎች ያመላክታሉ።

በእንሰት ተክል ላይ እየታየ ያለውን በሽታ ለመቅረፍ የተለያዩ መፍትሔዎች ቢቀመጡም ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የተቀናጀ ጥናት እና ምርምር ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑንም ይጠቁማሉ። በመሆኑም በእንሰት ላይ የሚከሰተውን በሽታ መቋቋም የሚችል አዲስ የእንሰት ዝርያ በጥናት መፍትሔ ከማፈላለግ አንጻር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብዙ ይጠበቃል። ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲም ባለፉት ዓመታት በምርምር ማዕከሉ ውስጥ ከአርሶ አደር ማሳ እየጠፋ ያለውን የእንሰት ዘሮችን የመጠበቅ ሥራ በልዩ ትኩረት በመሥራት ላይ ነው።

አቶ ዳንኤል መኖሬ (ረዳት ፕሮፌሰር ) በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በግብርና ሳይንስ ኮሌጅ የእጽዋት ትምህርት ክፍል መምህር እና ተመራማሪ ናቸው። ላለፉት ስድስት ዓመታት በእንሰት ላይ ምርምር ሲያካሄዱ ነበር፡፡ እናም ዩኒቨርሲቲው በእንሰት ተክል ላይ እየታየ ያለውን በሽታ ለመቅረፍ በርካታ ሥራ እየሰራ ይገኛል ይላሉ።



አቶ ዳንኤል እንደሚሉት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀዲያ ዞን ከአርሶ አደር ማሳ እንሰት የሚያጠፋ “እንሰት አጠውልግ” የሚባል በሽታ ተከስቷል። እንደሚታወቀው በዚህ አካባቢ እንሰት ከምግብነት ባለፈ ለጤና ጠቀሜታ እንዳለው፣ ድርቅን ለማቋቋምና የአፈር ለምነትን ከማምጣት አኳያ ብሎም ለእንስሳት መኖ ከመሆን ያለፈ ለበርካታ አገልግሎቶች የሚውለው ነው፡፡ እናም ይህን ውድ ሀብት ለመታደግ ዩኒቨርሲቲው በትኩረት እየሰራ ይገኛል።

አቶ ዳንኤል ዩኒቨርሲቲው በምርምር ማዕከሉ ውስጥ ከአርሶ አደር ማሳ እየጠፋ ያለውን የእንሰት ዘሮችን የመጠበቅ ሥራ በልዩ ትኩረት እየተሰራ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ ለዚህም ማሳያው የበሽታውን ዋና መንስኤ የመለየትና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ከመፈለግ አንጻር ጥናቶችን በማከናወን ላይ መሆኑ ነው። በተጨማሪም በሽታ የሚቋቋም የእንሰት ዝርያዎችን ለማግኘት ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ተቋማት ጋር እየሰራ መገኘቱ ነው ይላሉ።

ጥናቱ መሠረት በማድረግ የግብርና ሳይንስ ኮሌጅ ተመራማሪዎች ከምርምር ተቋማት ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር ከአካባቢው ጋር ሊላመድ (ሊስማማ) የሚችል የእንሰት ተክል ዘር ተከላ እየተካሄደ እንደሚገኝም ያስታወቁት ተመራማሪው፤ ከዚህም አንፃር ዩኒቨርሲቲው ከ86 በላይ የእንሰት ዝርያዎችን ከየአካባቢው ሰብስቦ ምርምር እያደረገ እንደሚገኝ አንስተዋል።

“የተተከሉ እንሰት ዓይነቶች ለመድኃኒትነት፣ ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ፣ በሽታ የሚቋቋሙ እና ለአካባቢ አየር ንብረት ጥበቃ የሚውሉ በአምስት ዓመት የሚደርሱ ዝርያዎች ናቸው። በዋናነት ጥምር እርሻን በመሬት ለማሳየት(Agro forestry system) በተጓዳኝ በዙሪያው ለተተከሉ የቡና ተክሎች ጥላ እንዲሆኑ ታስበው ሊተከሉ ችለዋል” ሲሉም ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲ ለአርሶ አደሩ የእንሰት ዝርያዎችን በምርምር ከማውጣት ባሻገር በአጠቃቀማቸው ዙሪያ የተለያዩ ሥልጠናዎች የተሰጠ መሆኑንም አስታውሰዋል።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፤ ለወደፊት ዩኒቨርሲቲው ከኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል ጋር በመሆን በባህላዊ መንገድ የነበረውን አድካሚውን ሂደት ለመቀነስ አዲስ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በአንድ ጊዜ ብዙ ችግኞችን በማባዛት ምርጥ ችግኝ እንዲስፋፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

በመጨረሻም በክልሉ በብዛት ለምግብነት የሚጠቀሙትን ውዱን ሀብት ለመታደግ ተቋሙ እያበረከተ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ ዩኒቨርሲቲው ከትኩረት አቅጣጫ አንዱ የሆነውን የአግሮ ፕሮሰስንግ ለማሳካት እየሠራ ያለው ሥራ በማድነቅ ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።

በጥቅሉ የእንሰት ተክል በብዛት ከሚመረትባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች ደቡብ ክልል ቀዳሚ ሲሆን፤ ተክሉ በሀገሪቷ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን የምግብ ፍጆታ እንደሚሸፍን ይገለጻል። ይሁንን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተክሉ ላይ የተከሰተው እንሰት አጠውልግ በሽታ በተክሉ ምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጥሯል። የእንሰት አጠውልግ በሽታ በ’ዛንቶሞናስ ካምቴስትሪስ ፓቶቫር ሙሳሴረም’ በሚባል የባክቴሪያ ተዋህስያን አማካኝነት የሚከሰትና በኢትዮጵያ ውስጥ እንሰትን ከሚያጠቁ በሽታዎች ዋንኛው እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህን ችግር በመከላከል ረገድ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ካለባቸው ኃላፊነት አንጻር ብዙ ይጠበቃል።

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲም ባለፉት ዓመታት በምርምር ማዕከሉ ውስጥ ከአርሶ አደር ማሳ እየጠፋ ያለውን የእንሰት ዘሮችን የመጠበቅ ሥራ በልዩ ትኩረት እየሰራ ነው። ዩኒቨርሲቲው በቀጣይም የእንሰት አጠውልግ በሽታ ለመከላከል በጥናትና ምርምር የታገዘውን ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ይታመናል። በተለይም የእንሰት ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የምርት ጥራትን ማሻሻል በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሰሩ ያሉት ሥራዎችን ማስቀጠል ይኖርበታል።